# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ | 82ኛ ዓመት ቁጥር 122 ጥር 2 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ





# "የቀለበት መንገድ ግንባታው በመቋረጡ ተጠቃሚ መሆን አልቻልንም"

- የአካባቢው ነዋሪዎች

# "ግንባታው በዚህ ጊዜ ይጀመራል ተብሎ የተቀመጠ ነገር የለም"

- የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- የቀለበት መንገድ ቀሪ ክፍል እና ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚገነባው የአዲሱ ገበያ-ሽሮሜዳ-ጃንሜዳ ጀርባ የመንገድ ግንባታ በመቋረጡ የንግድ እንቅስቃሴያችንን ማሳደግ አልቻልንም ሲሉ የአካባቢው ነዋሪዎች ቅሬታ አቅርበዋል። የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን በበኩሉ ግንባታው በዚህን ጊዜ ይጀመራል ተብሎ ቀን ገደብ አልተቀመጠለትም ብሏል፡፡

በአዲስ አበባ የአዲሱ ገበያ ነዋሪዎቹ አቶ ሰለሞን ባይህና ማሻ ሃብቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የቀለበት መንገድ ግንባታ አካል የሆነው የዊንጌት-አዲሱ ገበያ መንገድ በአማረ ሁኔታ ከተሠራ በኋላ ወደ ሽሮሜዳ የሚያልፈው መንገድ ግን ሳይሠራ ቆሟል።

በዚህ ምክንያት መንገዱ የሚያልፍበት መሬት ላይ የምንገኝ ሰዎች ቋሚ ግንባታ ለማከናወንም ሆነ የንግድ እንቅስቃሴያችን ለማከናወን ተቸግረናል ብለዋል።

የቀለበት መንገዱ ቢገነባ ለአካባቢው ማኅበረሰብ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ማደግ ጉልህ ሚና እንደሚኖረው ኅብረተሰቡ ያምናል። በዚህም ምክንያት ግንባታው እንዲጀመር ፍላጎት አለን። ለግንባታ ሥራውና አጠቃላይ ሂደቱም የአካባቢው ነዋሪ አስፈላጊውን ትብብር ለማድረግ ዝግጁ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

መንገዱ የሚያልፍበት የሽሮሜዳ አካባቢ ነዋሪዋ ወይዘሮ አልማዝ በቀለ በበኩላቸው፤ አካባቢው ለመንገድ ግንባታ በሚል ይፈርሳል ተብሎ ለረጅም ጊዜ ሲነገራቸው መቆየቱን ገልጸዋል።

ይሁንና የካሳ ክፍያ ሂደት በተመለከተም ከመንገድ ግንባታው ጋር በተያያዘ ምንም አይነት እንቅስቃሴ አለማየታቸውን አስረድተዋል።

"መንገዱ ቢገነባና ምን ያክል ሜትር ግቢዬን

"የቀለበት መንገድ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ዲያስፖራዎች በዓባይ ጉዳይ ጥናቶችን በማድረግ ለድርድር ግብዓት የሚሆኑ ሃሳቦችን ማቅረብ አለባቸው

ሞገስ ጸጋዬ

አዲስ አበባ፡- ዲያስፖራዎች በዓባይ ጉዳይ ጥናቶችን በማድረግ የሀገርን ጥቅም ለማስከበር በሚካሄደው ድርድር ላይ ግብዓት ማቅረብ እንዳለባቸው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ተስፋዬ ይልማ አስታወቁ፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ተስፋዬ ይልማ እንደገለጹት፤ በውጭ አገር በሚኖር ኢትዮጵያዊ ‹‹DEMYSTIFYING THE NILE›› በሚል ርዕስ የተጻፈው መጽሐፍ በዓባይ ጉዳይ ትልቅ ታሪክን የሚያስተላልፍና ለዲያስፖራዎች ጥንካሬን የሚሰጥ ነው፡፡

ዓባይን በተመለከተ በውጭ ሀገር ጸሐፊዎች ብዙ መጽሐፍት ይጽፋሉ ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ሆኖም በኢትዮጵያዊ ተመራማሪዎች ጥናት ተደርጎባቸው የተዘጋጁ አይደሉም ብለዋል፡፡

እንደ አምባሳደሩ ማብራሪያ፤ ይህ መጽሐፍ በኢትዮጵያዊ ዲያስፖራ መጻፉ ልዩ ያደርገዋል፡፡ ሁሉም



ፎቶ - ገባቦ ገብሬ

አምባሳደር ተስፋዬ ይልማ እና ዶክተር ደረጀ በፍቃዱ

ዲያስፖራ በሙያው፣ በችሎታው፣ በሥልጠናና በአቅም ግንባታው ዙሪያ ሀገሩን ማገዝ አለበት፡፡ በዓባይ ጉዳይ ጥናቶችን በማሰባሰብ መጽሐፍ መጻፍ በሌሎችም ጉዳዮች የሀገር ጥቅም ለማስከበር በሚካሄደው ድርድር ላይ ግብዓት ማቅረብ እንደሚገባም ገልጸዋል፡፡ መጽሐፉ በስፋት የተጻፈ በመሆኑ የተሳሳተ መረጃ ያላቸውን ሰዎች

ዲያስፖራዎች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






# በጦርነት ቀጠና ውስጥ የቆዩ ከተሞች በመጪዎቹ 15 ቀናት ሙሉ በሙሉ የኤሌክትሪክ ኃይል ያገኛሉ

ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ፡- በጦርነት የተጎዱ እና የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማቶቻቸው በመውደማቸው ምክንያት ኤሌክትሪክ ሳያገኙ የቆዩ ከተሞች በሁለት ሳምንታት ውስጥ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት አስታወቀ።

በጦርነት ቀጠና ውስጥ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# በላልይበላ የገና በዓል ከ1 ሚሊዮን በላይ ቱሪስቶች ተገኝተዋል

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- በቅዱስ ላልይበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ታኅሣሥ 29 ቀን 2015 ዓ.ም በተከበረው የእየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል ላይ ከ 1 ሚሊዮን በላይ ቱሪስቶች መገኘታቸውን የላልይበላ ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት አስታወቀ።

የቢሮው ቅርስ ጥበቃና ቱሪዝም ልማት ዲፓርትመንት አስተባባሪ አቶ ማንደፍሮ ታደሰ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በቅዱስ ላልይበላ ውቅር

በላልይበላ የገና በዓል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








ከ256 ሺ በላይ ለሚሆኑ ተመራቂ ተማሪዎች የመውጫ ፈተና ሊሰጥ ነው

ገጽ 3



ወይዘር ስመኝ ውቤ

## ኮሚሽኑ በ28 ተቋማት የዲጂታል አገልግሎት አሰጣጥ ተግባራዊ ማድረጉን አስታወቀ

ዳግማዊት አበበ

አዲስ አበባ፡- በ28 ተቋማት 50 አገልግሎቶችን ተደራሽ ያደረገ የኤሌክትሮኒክስ አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋቱን የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስታወቀ።

የኮሚሽኑ ምክትል ዋና ኮሚሽነር ወይዘሮ ስመኝ ውቤ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት በቅርቡ ብዙ መሥሪያ ቤቶች የኤሌክትሮኒክስ አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ላይ በቂ ሥልጠና ወስደው ወደ ተግባር ገብተዋል።

የኤሌክትሮኒክስ አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓቱ ተግባራዊ መደረጉ ተገልጋዮችን በማመላለስ የሚባክነውን ጊዜ፣ገንዘብና ጉልበት ከመቀነስ ባሻገር ተገልጋዮችን በማመላለስ እጅ መንሻ ለሚሹት ሰዎች ዕድል አይሰጥም ያሉት ምክትል ዋና ኮሚሽነሯ፤ ሥርዓቱ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ሲሆን በእያንዳንዱ መሥሪያ ቤት የሚሰጠው አገልግሎት የተገልጋዩን እርካታ ያማከለ ቀልጣፋና ዘመናዊ እንደሚሆንም ገልጸዋል። መሥሪያ ቤቶቹ በሙሉ አቅማቸው ወደ አሠራሩ እንዲገቡ ኮሚሽኑ በትኩረት እየሠራ መሆኑንም አመልክተዋል።

ቀደም ሲል የሀገሪቱንና የተቋማቱን ነባራዊ ሁኔታ ባላገናዘበ መልኩ የውጭ አገር ተሞክሮዎችን ወደ ሀገር አምጥቶ ለመተግበር የመሞከር ችግር እንደነበር ያነሱት ወይዘሮ ስመኝ፤ ነገር ግን አሁን ላይ ኮሚሽኑ የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓቱን ለማሻሻል እንደ በፊቱ የውጭ ተሞክሮ ብቻ ላይ ከመንጠልጠል ይልቅ ለአሠራር ምቹ የሆኑ ሀገር በቀል ተሞክሮዎችን እየተጠቀመ እንደሚገኝ ተናግረዋል። በተጓዳኝም ከአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚቀራረቡ ተሞክሮዎችንም ከውጭ በመውሰድ እንደሚጠቀምም አክለው ገልጸዋል።

የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት በተሳካ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ በተቋማት መካከል የቻርተር ስምምነት መፈራረማቸውን የገለጹት ምክትል ዋና ኮሚሽነሯ ፤ ማኅበረሰቡ አገልግሎት ለማግኘት ሲመጣ በቻርተሩ መሠረት ማሟላት ያለበትን ነገሮች አሟልቶ ቀድሞ አውቆ እንዲመጣ ይረዳዋል ብለዋል።

ኮሚሽኑ ብቻ ሳይሆን ሁሉም አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓቱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችላቸውን ሥልጠና ወስደው ወደ ሥራ እንዲገቡ መደረጉንና ለመናበብ እንዲመች ተቋማቱ ያዘጋጁት ቻርተር በኮሚሽኑ ዘንድ ማስመዝገባቸውንም ወይዘሮ ስመኝ አስታውቀዋል።

የቻርተሩ አዘገጃጀት እራሱን የቻለ ሂደት ያለው ሲሆን እንዴት ማዘጋጀት እንዳለባቸውና ከተዘጋጀ በኋላም እንዴት ወደ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ማምጣት እንዳለባቸው በሥልጠናው ተካቷል ብለዋል።

አክለውም እንደ የትራንስፖርት ሚኒስቴር አይነት ያሉ ተቋማት ይህን የአገልግሎት አሰጣጥ መንገድ ቀድመው አዘጋጅተው ወደ ኮሚሽኑ ያመጡ ሲሆን በአንጻሩ ብዙ የፌደራል መሥሪያ ቤቶች መዋቅር እየሠሩ በመሆናቸው ወደኋላ ቀርተዋል ብለዋል።

# ሚኒስቴሩ የዓሣ ሀብት ልማትን በቴክኖሎጂ በመደገፍ የሌማት ትሩፋትን ለማሳካት እየሠራ ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ያለውን ሰፊ የዓሣ ሀብት ልማት በቴክኖሎጂ በመደገፍ እንደ ሀገር የታቀደውን የሌማት ትሩፋት መርሐ-ግብር ስኬታማ ለማድረግ እንደሚሠራ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አስታወቀ።

በጋምቤላ ክልል ከ99 ሚሊዮን ብር በሚበልጥ ወጪ የተገነባው ዘመናዊ የዓሣ ማቀነባበሪያና የግብይት ቴክኖሎጂ ማዕከላት ፕሮጀክት ትናንት ተመርቆ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዶክተር በለጠ ሞላ እንደገለጹት፤ በሀገሪቱ ከሚገኙ ወንዞች፣ ሐይቆች፣ ኩሬዎችና ሌሎች የውሃ አካላት በዓመት ከ94 ሺህ 500 ቶን በላይ የዓሣ ምርት ማግኘት እንደሚቻል ጥናቶችን ዋቢ በማድረግ ጠቅሰዋል።

ሆኖም ያለውን እምቅ የዓሣ ሃብት በቴክኖሎጂ በማስደገፍ ለተጠቃሚዎች ከማድረስ ብሎም ወደ ኢኮኖሚያዊ ልማት ከመቀየር አኳያ ውስንነቶች መኖራቸውን ገልጸዋል።

ሚኒስትር መሥሪያ ቤቱ በዘርፉ የሚታየውን ክፍተት ግምት ውስጥ በማስገባት ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት በጋምቤላ ክልል ዘመናዊ የዓሣ ማቀነባበሪያና የግብይት ማዕከል መገንባት መቻሉን ገልጸዋል።

ፕሮጀክቱ በተለይም በቅርቡ በይፋ የተጀመረውን የሌማት ትሩፋት እውን ከማድረግ ባለፈ ከውጪ የሚገባውን የዓሣ ምርት በሀገር ውስጥ በመተካት በኩል የጎላ ፋይዳ አለው ብለዋል።

ሚኒስትር መሥሪያ ቤቱ በቀጣይም በሌሎች አካባቢዎች ተመሳሳይ ቴክኖሎጂዎችን ተደራሽ በማድረግ የዘርፉን ልማት ለማጠናከር እንደሚሠራ ዶክተር በለጠ አስታውቀዋል።

በሚኒስቴሩ የኢኖቬሽንና ምርምር ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ባይሳ በዳዳ በበኩላቸው በኢትዮጵያ ሕዝቡን በበቂ ሁኔታ መመገብ የሚያስችል የዓሳ ሀብት ቢኖርም በዓመት የሚመረተው ከ38 ሺህ ቶን አይበልጥም ብለዋል።



ዘመናዊ የዓሳ ማራቢያ ማዕከል

በዚህም ምክንያት ሀገሪቱ በዓመት ከ2 ነጥብ 5 ሚሊዮን ዶላር በላይ ወጪ በማድረግ የዓሣ ምርት ከውጪ እያስገባች እንደምትገኝ ገልጸዋል።

እንደ ጋምቤላ ክልልም በዓመት ከ12 ሺህ ቶን በላይ የዓሣ ምርት ማግኘት የሚቻል ቢሆንም አሁን ላይ እየተመረተ ያለው 5 ሺህ ቶን ብቻ መሆኑን ጠቁመዋል።

የተገነባው ዘመናዊ የዓሣ ማቀነባበሪያና የግብይት ማዕከል የክልሉን የዓሣ ሀብት በተሟላ መልኩ ለማልማት የሚያስችል መሆኑን ተናግረዋል። ማዕከሉ የቀዝቃዛ ሰንሰለቶችን ጨምሮ ዘመናዊ የዓሳ ማስገሪያ መሣሪያዎች፣ ጀልባዎችና ቀዝቃዛ ሰንሰለት የተገጠመላቸው የተሽከርካሪ ግብዓቶች የተሟሉለት መሆኑ ተገልጿል።

የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ኡሞድ ኡጁሉ በበኩላቸው በክልሉ በሚገኙ ወንዞችና ሐይቆች 113 ያህል የተለያዩ የዓሣ ዝርያዎች ያለበት አካባቢ ቢሆንም ዘርፉ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ባለመደገፉ በተፈለገው ልክ ሀብቱ ጥቅም ላይ እንዳልዋለ ተናግረዋል።

ይሁን እንጂ ከለውጡ ወዲህ የዓሣ ሀብትን በቴክኖሎጂ በመደገፍ ለክልሉ ብሎም ለሀገር ኢኮኖሚ ለማዋል ዘርፈ ብዙ ጥረቶች እየተደረጉ መሆኑን ተናግረዋል።

ለዚህም በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ድጋፍ ተገንብቶ በዛሬው ዕለት ለአገልግሎት የተዘጋጀው ዘመናዊ የዓሣ ማቀናበሪያና የግብይት ቴክኖሎጂ ማዕከል ዋነኛ ማሳያ ነው ብለዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በክልሉ ያለውን የዓሣ ሀብት ልማት በማዘመን ሀብቱ ለክልሉ ብሎም ለሀገር ጥቅም እንዲውል ላደረገው የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ ምስጋና አቅርበዋል።

የክልሉ ምክትል ርዕሰ መስተዳድርና የዓሣ ፕሮጀክቱ ስትሪንግ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ተንኩዋይ ጆክ የጋምቤላ ከተማን ጨምሮ በኢታንግና በአበቦ ወረዳ የተገነቡት የዓሣ ፕሮጀክቶች ከ99 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ እንደተደረገባቸው መናገራቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

ተመርቆ ለአገልግሎት የበቃው ዘመናዊ የዓሣ ማቀነባበሪያና የግብይት ቴክኖሎጂ ማዕከላት ፕሮጀክት ለአምስት ሺህ ወጣቶች የሥራ እድልን እንደሚፈጥርና ከ12 ሺህ ቶን በላይ የዓሣ ምርት ለማቅረብ ያስችላል ተብሏል።

# ለቀጣዩ የምርት ዘመን 12 ነጥብ 8 ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ግዥ ተፈጸመ

ማርቆስ በላይ

አዲስ አበባ ፡- ለ2015/16 የምርት ዘመን 12 ነጥብ 8 ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ግዥ መፈጸሙን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።

በሚኒስቴሩ የግብርና ኢንቨስትመንትና ግብዓት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ሶፊያ ካሳ እንደገለጹት፤ ግዥ ከተፈጸመው ከ12 ነጥብ 8 ሚሊዮኑ የአፈር ማዳበሪያ ውስጥ 500 ሺህ ኩንታሉ ዩሪያ መሆኑን ገልጸዋል።

ከታህሳስ 8 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ማዳበሪያውን የያዙ መርከቦች ወደ ጂቡቲ ማቅናታቸውን አመልክተው፤ ሁለት ማዳበሪያው ጭነው ጂቡቲ ወደብ ከደረሱት መርከቦችም 42 ሺህ ሜትሪክ ቶን ማዳበሪያ ወደ ኢትዮጵያ ማጓጓዝ መቻሉን ጠቅሰዋል።

በቀጣይ ቀናትም ሦስት ማዳበሪያ የጫኑ መርከቦች ጂቡቲ ወደብ ይደርሳሉ ያሉት ዶክተር ሶፊያ፤ ማዳበሪያው ቀድሞ ወደ ሀገር ውስጥ መግባቱ ከወዲሁ አርሶ አደሩ የሚፈልገው ማዳበሪያ መጠን በመግዛት ለእርሻ ሥራው ዝግጁ እንዲሆን ያስችላል ብለዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ማዳበሪውን ከውጭ ሀገር በግዢ እንደሚስገባ ጠቁመው፤ በዓለም ገበያ የማዳበሪያ ዋጋ ሲጨምር የሀገር ውስጥ የማዳበሪያ ዋጋም ይጨምራል። ዘንድሮም መጠነኛ ጭማሪ ይኖራል ብለዋል።

በባለፈው ዓመት የማዳበሪያ ዋጋ ከነበረበት ከአንድ ሺህ 800 ብር እስከ ሁለት ሺህ 200 ብር ጭማሪ አሳይቶ በ4 ሺህ 600 ብር ዋጋ ለአርሶ አደሩ በመቅረቡ ትልቅ መደናገጥ መፍጠሩን አውስተው፤ በወቅቱም መንግሥት 15 ቢሊዮን ብር ለማዳበሪያ ድጎማ ማድረጉን ተናግረዋል።




የግብርና ኢንቨስትመንትና ግብዓት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ሶፊያ ካሳ

በዘንድሮ ዓመት ካለፉት ዓመት ጋር ሲነጻጸር መጠነኛ የዋጋ ልዩነት ብቻ ያለው መሆኑን በማንሳት፤ማዳበሪያው ግዥ የተፈጸመበት ዋጋ በቅርቡ ይፋ እንደሚሆንም ነው የገለጹት።

በአርሶ አደሩ ላይ የማዳበሪያ ዋጋ ሲጨምር በምርት ዋጋ ጭማሪ እንደሚኖረው የገለጹት ዶክተር ሶፊያ፤ ይህም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የከተማውንም ሆነ የገጠሩ ማኅበረሰብ የዋጋ ንረትን ስለሚያባብስ ለዚህም ሲባል በባለፈው ዓመት መንግሥት ለማዳበሪያ ድጎማ ማድረጉን ነው የገለጹት።

የሽያጭ ዋጋውን በተመለከተ ዓለም አቀፍ ዋጋውን መሠረት አድርጎ እንደሚከናወንም አመልክተው፤የዚህ ዓመት የሽያጭ ዋጋን በተመለከተም በቅርቡ ይፋ እንደሚደረግ ጠቅሰዋል። በተጨማሪም አርሶ አደሩ የተፈጥሮ ማዳበሪያ እንዲጠቀም ግብርና ሚኒስቴር ክትትል ያደርጋል ብለዋል።

# ከ256 ሺ በላይ ለሚሆኑ ተመራቂ ተማሪዎች የመውጫ ፈተና ሊሰጥ ነው

**ማሕሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡ -በመጪው ሰኔ ወር ከ256 ሺ በላይ ለሚሆኑ የከፍተኛ ትምህርት ተመራቂ ተማሪዎች የመውጫ ፈተና ለመስጠት በቂ ዝግጅት እየተደረገ እንደሆነ የትምህርት ሚኒስቴር ገለጸ። ያነጋገርናቸው ተመራቂ ተማሪዎችም ለመውጫ ፈተናው ዝግጅት እያደረጉ መሆኑን ገልጸዋል።

በትምህርት ሚኒስቴር አካዳሚክ ጉዳዮች መሪ ሥራ አስፈጻሚ ዶክተር ኤባ ሚጀና ለኢትዮጵያ ፕሬስ እንደገለጹት፤ ከመንግሥት ከፍተኛ ተቋማት 146 ሺ እና ከግል ከፍተኛ ተቋማት 110 ሺ በድምሩ 256 ሺ ተመራቂ ተማሪዎችን የመውጫ ፈተና ለመስጠት የሚያስችል መመሪያ ሰነድ ከማዘጋጀት ጀምሮ ለፈተናው የሚያስፈልጉ ነገሮችን የማሟላት ሥራ እየተሠራ ነው ።

በዩኒቨርሲቲዎች ያለውን የኮምፒዩተር አቅርቦት እና የተፈታኞች ብዛት በመለየት የመውጫ ፈተናውን በኦንላይን ለመስጠት ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን አመልክተው፤ በዚህም ተመራቂ ተፈታኞች ውጤቱን ወዲያው የሚያሳውቅ ሶፍት ዌር ለማዘጋጀት እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል። በቀጣይ ጥያቄዎቹን ወደማዘጋጀት እንሄዳለን ብለዋል ።

ስለ የመውጫ ፈተናው የሚመለከቱ መረጃዎችንም በየዩኒቨርስቲዎቹ ባሉ በተማሪ ኅብረቶች በኩል እንዲሁም ማኅበራዊ ድረገጽን በመጠቀም



ዶክተር ኤባ ሚጀና

ለተፈታኝ ተማሪዎችም ተደራሽ እንዲሆን ተሠርቷል። ዩኒቨርሲቲዎች ተማሪዎችን አጋዥ የትምህርቶች ሞጅሎችን ከማዘጋጀት ጀምሮ ፈተናውን ለመውሰድ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን የማዘጋጀት ሥራ እየተሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

እንደ ዶክተር ኤባ ገለጻ፤ የከፍተኛ ትምህርት መውጫ ፈተና ከተለያዩ ያደጉት ሀገራት ተሞክሮ ተወስዶ ነው የተዘጋጀው፤ ይህ የመውጫ ፈተና ለተማሪው በየዓመቱ የተማረውን ትምህርት ምን ያህል አውቆት እንዳለፈ ራሱን የሚፈትሽበትና ብቁ መሆኑን የሚያረጋግጥበት ይሆናል ። የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል ያግዛል። ዩኒቨርሲቲዎች ደግሞ ባበቁት ተማሪ ልክ እውቅና የሚያገኙበት ሁኔታን ይፈጥራል ።

የመውጫ ፈተናው እንደሚሰጥ ያሳወቅነው ከዓመት በፊት በመሆኑ ለተመራቂ ተፈታኝ ተማሪዎች በቂ የዝግጅት ጊዜ ይኖራል ብለን እናስባለን ያሉት ዶክተር ኤባ፤ ለፈተናው መሳካት ከኢትዮ ቴሌኮምና ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት ጋር በቅንጅት እንሠራለን ብለዋል።

በድሬዳዋ ዩኒቪርሲቲ የጆርናሊዝም ተማሪው በቃሉ ግርማ ሰኔ ወር 2015 ዓ.ም ላይ ለሚሰጠው የመውጫ ፈተና ዝግጅት እያደረገ እንደሆነ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ተናግሯል። እንደ ተማሪ በቃሉ ገለጻ ፤ፈተናው በኦንላይን መሰጠቱ ከወገንተኝነት የጸዳ መንገድ ያደርገዋል። ለተመራቂ ተማሪዎችም ብቁ እና በሙያው ሙሉ ዕውቀት ይዘው እንዲወጡ ያደርጋል።

ተማሪ በቃሉ ለፈተናው በግል እና ከመምህራን ድጋፍ እየተደረገላቸው መሆኑን ገልጾ፤ ተማሪው እንዲዘጋጅ የተሰጠው ጊዜ ግን አነስተኛ ነው ብሏል።

ሌላዋ ተመራቂ ተማሪ የደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ ራሄል መኮት ስለፈተናው አሰጣጥ በተለያየ መንገድ አውቀናል። ከመምህራን የተለያዩ ድጋፎች እየተደረገ ቢሆንም ለፈተናው የሚረዱ የድጋፍ ኮርሶች እና በቂ አቅርቦት መኖር አለበት ብላለች።

እንደ ተማሪ ራሄል ገለጻ ፈተናው በግቢ ቆይታ ያገኙትን እውቀት ለመመዘንና ከተመራቂዎች ጋር ተወዳዳሪ በመሆን የሥራ ዕድል እና በራስ መተማመንን ለማሳደግ ይጠቅማል።



አቶ መስፍን ጉብላ

# በዞኑ ለመጀመሪያ ጊዜ ከ5 ሺህ በላይ ሄክታር የበጋ መስኖ ስንዴ ለማልማት እየተሠራ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

ሚዛን አማን፡- በቤንች ሸኮ ዞን የተለያዩ ወረዳዎች ዘንድሮ 5 ሺህ 41 ሄክታር ስንዴ ለመጀመሪያ ጊዜ በበጋ መስኖ እየለማ መሆኑን የዞኑ ግብርና መምሪያ አስታወቀ።

በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት የቤንች ሸኮ ዞን ግብርና መምሪያ ኃላፊ አቶ መስፍን ጉብላ እንደተናገሩት፤ በቤንች ሸኮ ዞን ወረዳዎች አርሶ አደሩን በምግብ እህል እራስን ለማስቻል እንዲያግዝ እንዲሁም ስንዴን ለውጪ ገበያ መላክ እንዲቻል ዘንድሮ ለመጀመሪያ ጊዜ ስንዴ በበጋ መስኖ እየለማ ነው።

ቤንች ሸኮ ዞን ከዚህ በፊት አርሶ አደሩ ስንዴን በበጋ መስኖ የማልማት ልማድ ያልነበረው ቢሆንም አሁን መንግሥት በያዘው አቅጣጫ መሠረት በዞኑ ምቹ ቦታዎች መረጣ ተካሂዶ በበጋ ስዴን በመልማት ላይ ይገኛል።

በዚህም የቤንች ሸኮ ዞን ግብርና መምሪያ በዚህ ዓመት ብቻ በበጋ መስኖ 5 ሺህ 41 ሄክታር መሬት በማልማት ወደ 2 ሺህ 52 ኩንታል ስንዴ ለማምረት ዕቅድ ይዞ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል።

አርሶ አደሩ የበጋ መስኖ ስንዴ እያለማ ያለው በኩታ ገጠም ነው ያሉት የመምሪያው ኃላፊ አቶ መስፍን፤ እስከ አሁን ከ3 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት መታረሱንና ከተጠቀሰው መጠንም ከግማሽ በላይ መሬት በዘር መሸፈን መቻሉን አብራርተዋል።

ሰብሉ በአሁኑ ወቅት ጥሩ በሚባል ደረጃ ላይ መድረሱንና ቀሪው መሬትም በጥቂት ጊዜያት በዘር እንደሚሸፈን አክለው ገልጸዋል።

በዞኑ ዘንድሮ ከ5 ሺህ 41 ሄክታር በላይ መሬት ላይ ስንዴን በመስኖ ለማልማትና በቀጣዩ ዓመት ደግሞ ይህን ለማሳደግ መታቀዱን የገለጹት ኃላፊው፤ አርሶ አደሩ መስኖን በመጠቀም ለመጀመሪያ ጊዜ በኩታ ገጠም አሠራር በሚከናወነው የስንዴ ልማት መንግሥት የውሃ መሳቢያ ፓምፖች እና የምርት ግብዓት የማሟላት ሥራ ማከናወኑን ተናግረዋል።

በዚህም ወጣቱን ወደ እርሻ ሥራ በማስገባት በምግብ ሰብል እራሱን እንዲችልና በአንድ ቦታ ተረጋግቶ በመኖር ቋሚ የሆነ የተሻለ ሕይወት እንዲመራ ያስችለዋል ብለዋል።

በተለይ በአሁኑ ወቅት በዞኑ አስተማማኝ ሰላም መኖሩን የጠቆሙት አቶ መስፍን፤ ካለው ሰፊ መሬት ጋር በተያያዘ በግብርና መስክ መሳተፍ ለሚፈልጉ ባለሀብቶች ምቹ ሁኔታ እንዳለ ተናግረዋል።

በተመሳሳይ ቤንች ሸኮ ዞን ወደ 154 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በቡና ማሳ ተሸፍኗል። ከቡና ቀጥሎ ዞኑ በሚታወቅበት የፍራፍሬ ምርትም ከ40 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት መሸፈኑንና አካባቢው ለቅመማ ቅመም ምርት ምቹ በመሆኑ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑንም ኃላፊው አብራርተዋል።

# የሰላም ስምምነቱ ዘርፉን እያነቃቃ መሆኑን በአክሱም ከተማ የሆቴል ባለቤቶች ገለጹ

**አዲሱ ገረመው**

አክሱም፡- የሠላም ስምምነቱ የአክሱም ከተማን የሆቴል ቱሪዝም እያነቃቃ መሆኑን የከተማዋ የሆቴል ባለቤቶች ገለጹ።


በአክሱም ከተማ የያሬድ ዜማ ኢንተርናሽናል ሆቴል ባለቤት አቶ አባይ ክንፈ ከኢፕድ ጋር ባደረጉት ቆይታ፤ ከጦርነቱ በፊት በሆቴልና ቱሪዝም መስክ በአክሱም ከተማ ትልቅ ሥራ ይሠራ እንደነበር ገልጸዋል። በተለይ ከአዲስ ዓመት እስከ የካቲት መጨረሻ ባሉት ወራት በርካታ የውጭ አገር ቱሪስቶች ለጉብኝት ወደ አካባቢው ይሄዱ እንደነበርም አንስተዋል። ከጦርነቱ ጋር ተያይዞ ሆቴሎች ላለፉት ሁለት ዓመታት መጎዳታቸውን በመጥቀስ፤ የተጀመረው የሰላም ሰምምነት ዘርፉን ዳግም ሊያነቃቃው እንደሚችል አስታውቀዋል።

እንደ አቶ አባይ ገለጻ፤በጦርነቱ ሳቢያ የሆቴል እንቅስቃሴ ባለመኖሩ ዘርፉ ተጎድቷል። አገልግሎቱ ሙሉ ለሙሉ በመቆሙ ሠራተኞችም ጭምር ብዙ ችግር ደርሶባቸዋል ብለዋል።

የያሬድ ዜማ ኢንተርናሽናል ሆቴል ከ80 በላይ ሠራተኞችን ቀጥሮ ይሠራ የነበረ ቢሆንም፤ በጦርነቱ ምክንያት ሁሉም ሠራተኞች ከሥራ ውጭ ሆነው ቆይተዋል። በወቅቱ ሠርቶ ገንዘብ ከማግኘት ይልቅ የሕይወት ጉዳይ አሳሳቢ ሆኖ ቆይቷል ሲሉም ተናግረዋል።

ሆቴሉ የባንክ እዳ ያለበት እንደመሆኑ ለረጅም ጊዜ ያለ ሥራ መቆየቱ አሳሳቢ ሆኖ እንደቆየ የተናገሩት አቶ አባይ፤ ከሰላም ስምምነቱ ወዲህ ሆቴሉን ዳግም ሥራ ለማስጀምር ጥረት እየተደረገ እንደሆነ ገልጸዋል።

ሰላሙ የጸና ከሆነ በአክሱም ያሉ ሆቴሎች ዳግም አገግመው ወደ ሥራ ለመግባት ትልቅ ዕድል ያገኛሉ ያሉት አቶ አባይ፤ ሰላሙ የአካባቢውን የሆቴል ቱሪዝም እንደሚያነቃቃም ገልጸዋል።





በጦርነቱ ምክንያት ጉዳት ቢደርስም ወደ አገልግሎት ለመመለስ ሙሉ የሥነ ልቦና ዝግጅት እንዳለም ጠቁመዋል። ተበታትነው የነበሩ ሠራተኞችን ወደ ሥራ የመመለስና ተተኪ ግብዓቶችን የሚሟላት ሥራዎችን ለማከናወንም በእንቅስቃሴ ላይ እንዳሉ አስታውቀዋል።

የሰው ልጅ ሀብቱ ሰላም ነው ያሉት አቶ ዓባይ፤ ከሰላም ስምምነቱ ወዲህ በሁሉም መስኮች ያሉ እንቅስቃሴዎች የመጪውን ጊዜ በጎ ተስፋ አመላካች እንደሆኑ ገልጸዋል። አካባቢው የቱሪስት መዳረሻ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ መንግሥት ያለፈውን ወቅት ችግር አይቶ ሆቴሎቹ የሚንቀሳቀሱበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር ይኖርበታል ሲሉም ተናግረዋል።

አቶ ዓባይ እንዳሉት፤ አክሱም በአብዛኛው እንቅስቃሴው በቱሪዝም ላይ የተመሠረተ ነው። በአካባቢው ያሉ ሆቴሎችም የዚህ ዕድል ተጠቃሚ ናቸው። አሁን ላይ ነዋሪውም ሆነ ተቋማት ዳግም ወደ እንቅስቃሴያቸው የሚመለሱበት ጊዜ ነው። የሰላሙ ስምምነት ለከተማዋ የቱሪዝም እንቅስቃሴ ተስፋ ሰጪ ነው።

የሮማዲ ሆቴል አክሱምና መቐለ ባለቤት አቶ ምዑዝ አብርሐ በበኩላቸው፤ጦርነቱ በአክሱም በሆቴል ቱሪዝም ላይ ያሳረፈውን ጫና መቋቋም ከባድ እንደሆነ ገልጸዋል። ሆቴሎች ከአገልግሎት ውጭ በመሆናቸው በርካታ ሠራተኞችም ከሥራ ውጭ ተደርገው እንደነበር ጠቅሰዋል። ሆቴሉ ሥራ ባለመሥራቱ የባንክ ዕዳን ጭምር ይዞ እንደቆየና ይህም አሳሳቢ እንደሆነ ተናግረዋል።

ሆቴሎች አገልግሎት አቁመው መቆየታቸው አገሪቷ ከዘርፉ የምታገኘውን ገቢ እንዳሳጣትም አቶ ምዑዝ ተናግረዋል። ከሰላም ስምምነቱ ወዲህ ሆቴሉ በከፊል ወደ አገልግሎት እንደተመለሰና ግማሽ ያህል ሠራተኞችንም ሥራ እንዳስጀመረ ገልጸዋል። የተጀመረው የሰላም ሂደት ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ሲደረግ ሆቴሎች ዳግም ወደ ሥራ ገብተው አገልግሎት መጀመር እንደሚችሉና ዘርፉም የተነቃቃ እንደሚሆን ተስፋቸውን ተናግረዋል።

# ሀገር በቀል የኮንስትራክሽን ተቋራጮችን አቅም ለማሳደግ እየተሠራ ነው

ኢያሱ መሰለ

አዲስ አበባ፡- አገር በቀል የኮንስትራክሽን ተቋራጮችን የመፈጸም አቅም ለማሳደግ ያግዛሉ የተባሉ ሦስት ሥርዓቶችን ይፋ አድርጎ በሕግ ማዕቀፍ ለማካተት እየተሠራ መሆኑን የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት አስታወቀ።

የኢንስቲትዩቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ዳዊት መሐሪ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት ተቋሙ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለመቅረፍ የአሠራር ሥርዓቶችን የማስፈን፣ ሥልጠናዎችን የማዘጋጀትና ቴክኖሎጂዎችን የማላመድ ሥራዎችን ይሠራል። በዚሁ መሠረት የሀገር አቀፍ ተቋራጮችን የመፈጸም አቅም ለማሳደግ የሚረዱ ጥናቶችን አስጠንቷል።

ተቋሙ በንዑስ ተቋራጮች (sub contructing )፣ በሽርክና (joint veneture) እና በግል ስምምነት (local partnership) ላይ የተደረጉ ጥናቶችን በሕግ ማዕቀፍ አካቶ ሥራ ላይ ለማዋል በሙያተኞች እያስተቸ ይገኛል። በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የከተማ መሠረተ ልማትና ትራንስፖርት ቋሚ ኮሚቴ አባላትም በጉዳዩ ዙሪያ ሀሳብ እንዲሰጡ ተደርጓል።

ሕጉ ትልልቅ ተቋራጮች ከትንንሽ ተቋራጮች ጋር የሚያደርጉት ውል ሕጋዊ የአሠራር ሥርዓትን ተከትሎ እንዲፈጸም የሚያስገድድ መሆኑን ዳይሬክተሩ ጠቅሰው፤ የንዑስ ተቋራጭነት ሥራ እስከ ዛሬ ድረስ ዋና ተቋራጩና ንዑስ ተቋራጩ በሚያደርጉት የዕርስ በዕርስ ውልና ስምምነት ላይ ተመሥርቶ ይፈጸም ነበር ብለዋል።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ ሁለቱም በውላቸው መሠረት ባይፈጽሙ የስምምነታቸውን ጉድለት ተከትሎ ተጠያቂ የሚያደርጋቸው ሕግ አልነበረም። አሁን የተጠናው ጥናት ይህንን ችግር የሚፈታ ነው። በረቂቅ ደረጃ የተዘጋጀው ሕግ ከዋና ተቋራጩ ላይ ከ30 እስከ 40 በመቶ የሚሆነውን ሥራ ለንዑስ ተቋራጮች እንዲሰጥ የሚያደርግ ነው። ይህም ጨረታውን ተወዳድረው ማሸነፍ ለማይችሉ ንዑስ ተቋራጮቹ የሥራ ዕድል ይፈጥራል።

በሽርክና (joint venture) ልምድና አቅምን አዋሕዶ



አቶ ዳዊት መሐሪ

ውጤታማ ሥራ ለመሥራት የሁለት ተቋራጮችን ጊዜያዊ ጥምረት የሚያበረታታውን ጥናት በሕግ ማዕቀፉ ለማካተት እየተሠራ እንደሆነ ጠቅሰው፤በተናጠል ያላቸው አቅም ለፕሮጀክቱ ብቁ የማያደርጋቸው ሽርክና ፈጥረው ፕሮጀክቱን እንዲሠሩ ዕድል የሚፈጥርና እንደውላቸው መሠረት ተጠያቂ የሚያደርግ ነው ብለዋል።

ከዚህ በፊት ሽርክናን ተግባራዊ ለማድረግ የተዘጋጀ መመሪያ እንደነበር ያስታወሱት ዳሬክተሩ መመሪያው በሕግ ማዕቀፍ ሥር ባለመግባቱ ተግባራዊነቱ ላይ ክፍተቶች ነበሩበት ብለዋል። አሁን የተጠናውን ጥናት በሕግ ማዕቀፍ ውስጥ ማካተት ያስፈለገበት አንዱ ምክንያት እንዲህ አይነት ችግሮችን ለመፍታት ነው።

አብዛኛዎቹ ግዙፍ ፕሮጀክቶች በውጭ ተቋራጮች እየተያዙ መምጣታቸውን የተናገሩት ዳይሬክተሩ፤ አዲሱ ጥናት የውጭ ተቋራጮች የሀገር ውስጥ ተቋራጮችን እንዲያሳትፉ የሚያስገድድ እንደሆነም አብራርተዋል። የሀገር ውስጥ ተቋራጮች በሥራ ውስጥ እንዲቆዩ የሚያደርግ፣የሥራ ልምድ የኢኮኖሚ አቅምና የቴክኖሎጂ ዕውቀት አግኝተው በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ላይ ተጽዕኖ ፈጣሪ እንዲሆኑ የሚያስችል ነው። ሕጉ አገር በቀል ተቋራጮች እርስ በእርሳቸው ብቻ ሳይሆን ከውጭ ተቋራጮችም ጋር በሽርክና እንዲሠሩ ዕድል የሚሰጥ ነው።

ተቋሙ ከወራት በፊት በተለያዩ ዘርፎች አራት ጥናቶችን አስጠንቶ በባለሙያዎች በማስተቸት ወደ ሥራ ለማስገባት እየተንቀሳቀሰ መሆኑንም አቶ ዳዊት ገልጸዋል።



## በላልይበላ የገና በዓል...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አብያተክርስቲያናት በተከበረውን የገና በዓል ላይ ከ፤ ሚሊዮን በላይ ቱሪስቶች ታድመዋል።

በሰሜኑ ጦርነት የተነሳ የገና በዓልን ባለፉት ሁለት ዓመታት በላልይበላ ከተማ በደማቅ ሁኔታ ማክበር እንዳልተቻለ አስታውሰው፤ የዘንድሮው በዓል ግን በተሳካና በሰላማዊ ሁኔታ በደማቅ ሥነ ሥርዓት ታጅቦ መካሄዱን አስታውቀዋል።

እንደ አቶ ማንደፍሮ ገለጻ፤ በበዓሉ በተሳተፉ ቱሪስቶች አማካኝነት የአገልግሎት ዘርፉም የተሻለ ገቢ እንደተፈጠረለት ይታመናል። በተለይ ሆቴሎች፣ ምግብና መጠጥ አቅራቢ ድርጅቶች እንዲሁም አስጎብኚዎች በኮቪድና በጦርነቱ ምክንያት ተዳክሞ የነበረው ሥራቸው መነቃቃት ተፈጥሯል ብለዋል።

ወደላልይበላ የመጡት ቱሪስቶች ከተለያዩ ሀገራት የመጡ መሆናቸውን የገለጹት አቶ ማንደፍሮ፤ ከበዓሉ አከባበር ባለፈ ጎብኚዎች በከተማዋ የሚገኙ ቅርሶችን ተዘዋውረው እንዲጎበኙ ጥረት መደረጉን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም በኢትዮጵያ የሚገኙ የተለያዩ ሀገራት አምባሳደሮችና የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች በዓለም ቅርስነት በተመዘገበው የላልይበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ተገኝተው በዓሉን በማክበራቸው የተነሳ የቱሪዝም ዘርፉ ገቢ እንዲያድግ ትልቅ ዕድል ተፈጥሯል ብለዋል።

የከተማዋና አካባቢው ሕዝብ እንዲሁም የጸጥታ አካላት ቱሪስቶች ወደላልይበላ ገብተው እስኪወጡ ድረስ አስፈጊውን ትብብር በማድረግ የነበራቸው ሚና ከፍተኛ ነው። ሕዝቡም እንግዳ ተቀባይነቱን በድጋሚ ያሳየበት አጋጣሚ ስለነበር በርካታ ቱሪስቶች ተደስተው መመለሳቸውን ገልጸዋል ሲሉ አቶ ማንደፍሮ አስረድተዋል።

በላልይበላ የገና በዓል ከተሳተፉ ጎብኚዎች መካከል አንዱ የሆኑት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የቻይና ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር ዛሃኦ ዚዩኣን የገናን በዓል በላልይበላ ካሳለፉ በኋላ በትዊተር ገጻቸው ባሰፈሩት መልዕክት በዩኔስኮ የዓለም ቅርስነት በተመዘገበው ላልይበላ በነበረኝ የሁለት ቀናት ቆይታ የኢትዮጵያውያን ወዳጃዊና የሚስብ እንግዳ ተቀባይነት አስደንቆኛል ብለዋል።

በላልይበላ ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ መረጃ መሠረት፤ ከዚህ ቀደም በነበሩ የገና በዓል ላይ ወደላልይበላ እስከ ፤ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ቱሪስቶች በየዓመቱ በበዓሉ ይሳተፉ ነበር። በዘንድሮው በዓል ላይ የተመዘገበው የቱሪስቶች ቁጥር ከእስካሁኖቹ የገና በዓላት ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛው ሆኖ ተመዝግቧል።

## በጦርነት ቀጠና ውስጥ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በሰሜን ዲስትሪክት ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ብዙወርቅ ደምሴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍሎች በነበሩ ጦርነቶች በተለያዩ ክልሎች የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማቶች ውድመት ደርሷል። በተለይ በአማራ፣ አፋር እና ትግራይ ክልሎች በሚገኙ ከተሞች የመብራት አገልግሎት ተቋርጦ ቆይቷል።

አገልግሎቱን ወደነበረበት ለመመለስ የተለያዩ ሥራዎች ሲከናወኑ የቆዩ ሲሆን፤ በአሁኑ ጊዜ በአማራ፣ አፋር እና ትግራይ ክልሎች በጦርነት ምክንያት በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል በነበረው ግጭት ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸውን ከተሞች የመብራት አገልግሎት በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ወደ ነበረበት ለመመለስ በትኩረት እየተሠራ ነው።

እንደ አቶ ብዙወርቅ ገለፃ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በተጠቀሱት ክልሎች በዞንና በወረዳ ደረጃ ግጭት በተከሰተባቸው አካባቢዎች የሚገኙ 59 ዋና ዋና ከተሞች የተከሰተውን የኤሌክትሪክ አገልግሎት እጦት ለመፍታት አቅዶ ሲሠራ ቆይቷል። ከእነዚህ ከተሞች አብዛኞቹ የመብራት አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል። ቀሪዎቹ ደግሞ በሁለት ሳምንታት ውስጥ ያገኛሉ።

ኃላፊው አብነት አንስተው እንዳስረዱትም፤ በትግራይ ክልል ሽራሮ አካባቢ የመብራት መሠረተ ልማቱ በደረሰበት ከባድ ጉዳት ምክንያት ለጥገና ሁለት ሳምንታትን ይወስዳል። በተጨማሪም አንዳንድ በአማራ ክልል የሚገኙ ከተሞች በተለይም ሳተላይት ከተማ እየተባሉ የሚጠሩ የገጠር ከተሞች በጣም ርቀው የሚገኙ በመሆናቸው በተመሳሳይ በ15 ቀናት ጊዜ ውስጥ የኤሌክትሪክ አገልግሎት መልሰው ያገኛሉ።

በአፋር ክልል እንደ ኩነማ ያሉ የመብራት አገልግሎት ያጡ ቀሪ ከተሞች ከሦስት እስከ አራት ቀናት ባለው ጊዜ ውስጥ የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ይሆናሉ ብለዋል።

በተለይ የወልድያ ሰብስቴሽን በመዘረፉ አንዳንድ በአፋር ዞን የሚገኙ እንደ ጭፍራ፣ ሰናኤ እና አውራ የመሳሰሉ ከተሞች አሁንም የኤሌክትሪክ አገልግሎት ማግኘት አልቻሉም። ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በዚህ አካባቢ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ኤሌክትሪክ አገልግሎትን ወደ ነበረበት ለመመለስ የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውን መቆየቱን ኃላፊው ተናግረዋል።

በተመሳሳይም የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት ውድመትን ያስከተለውን ግጭት ተከትሎ ከሁለት ዓመት በላይ ተቋርጦ የነበረው የአባብአላ ከተማና አካባቢው የኤሌክትሪክ ኃይል አግኝቷል።

ጦርነቱ በተከሰተባቸው አካባቢዎች የኤሌክትሪክ ኃይል ወደነበረበት ለመመለስ ሌብነት፣ የመሠረተ ልማቶች ውድመት፣ የተቀበሩ ፈንጂዎች እና መሰል ችግሮች እንቅፋት ሆነው የቆዩ መሆናቸውንም ኃላፊው አስረድተዋል።

## ዲያስፖራዎች በዓባይ ጉዳይ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ያርማል፤ ዲፕሎማሲያዊ ጫናዎችን ይቀንሳል ሲሉ ገልጸዋል።

የሚቀጥለው ትውልድ የጎደለውን እያሟላ በዓባይ ጉዳይ ሰፊ መረጃ እንዲኖረው የሚያደርግ የጥናት ሥራ መሆኑንም በመግለጽ፤ እምቅ እውቀት ያላቸው በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ ሥራ መሥራት እንዳለባቸው አሳስበዋል።

የመጽሐፉ አዘጋጅ በፍሎሪዳ ዩኒቨርሲቲ ምክትል ፕሬዚዳንትና በናይል ሃውስ የምርምር ባልደረባ ዶክተር ደረጄ በፍቃዱ እንደገለጹት፤ ስለ ዓባይ ለማወቅ የዓባይን ታሪክ ማወቅና ማስረዳት ያስፈልጋል።

በዓባይ ጉዳይ የሚጻፉ መጽሐፍት በብዛት ከግብጽ ወይም ከእንግሊዝ በኩል በመሆናቸው ስለ ዓባይ ያለው ሌላ አይነት ገጽታ ነው። በርካቶችም የተሳሳተ መረጃ እንዲኖራቸውም ሆኗል። መጽሐፉ ዓባይ ላይ ያለውን የኢትዮጵያን ታሪክን በማስረዳት በዓባይ ውሃ ላይ የሚገነባው ግድብ አግባብ መሆኑን ለማስረዳት ይጠቅማል ብለዋል።

ከዚህ በፊት በትክክል መረጃዎች ተሰባስበው ስላልቀረቡ ምዕራባውያን ከግብጾች በኩል የተጻፉ መጽሐፍትን ብቻ በማንበብ በኢትዮጵያ ላይ ጫናዎችን ሲያደርጉ ነበር ብለዋል። ስለ ዓባይ ጥናቶች መታተማቸው በዓባይ ዲፕሎማሲ ላይ አወንታዊ ተጽዕኖ እንዲኖር ያደርጋል ብለዋል።

መጽሐፉ ስድስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን የዓባይን ታሪክና ጂኦፖለቲክ፣ በዓባይ ግድብ የተካሄዱ ከ27 በላይ ስምምነቶች፣ ስለ ሳይንሱ፣ ከተፋሰስ አገራት ጋር ስላለው ግንኙነት፣ ስለ ግድቡ አሠራርና ጥራት ያካተተ በመሆኑ ለኅብረተሰቡ ሰፊ መረጃን በመስጠት የተስተካከለ ግንዛቤ እንዲፈጠር ያደርጋል ብለዋል።

እንዲህ አይነት ሥራዎች የዲፕሎማሲ ሁኔታውም እንዲስተካከል ይረዳል ያሉት ደራሲው፤ ዲያስፖራዎች በችሎታቸው ሀገራቸውን እንዲረዱ ኤምባሲዎች ጠንካራ ሥራ መሥራትና ማስተባበር እንደሚገባቸው አሳስበዋል። ዲያስፖራው ያለውን የሀገር ፍቅር ወደ ተግባር እንዲለውጥ ከተደረገ ከኢትዮጵያ አልፎ አፍሪካን ማልማት የሚችል አቅም መኖሩንም ገልጸዋል።

## “የቀለበት መንገድ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንደሚነካው ባውቅ እኔም በያዝኩት መሬት ላይ ምን መሥራት እንዳለብኝ ልወስን እችላለሁ። ይሁንና በግቢዬ ቋሚ ግንባታ ለማከናወን እንኳን እርግጠኛ የሆነውን ጉዳይ ባለመለየቴ ሳልወስን ቆይቻለሁ” ሲሉ አስረድተዋል።

ለአካባቢው ብሎም ለከተማዋ ሰፊ ጥቅም የሚሰጠው የመንገድ ፕሮጀክቱ ቢገነባ ምርጫዬ ነው ያሉት ወይዘሮ አልማዝ፤ ካልሆነ ደግሞ መንገዱ መቋረጡ ቢገለጽ ወይንም ግንባታው የሚጀመርበት ትክክለኛ ቀን ለኅብረተሰቡ ግልጽ ቢደረግ የተሻለ ነው ሲሉ ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን ምክትል ዳይሬክተር ኢንጂነር ታከለ ሉለና በበኩላቸው እንደገለጹት፤የመንገድ ግንባታው ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ በመሆኑ በአንድ ጊዜ ይሠራል ተብሎ አይጠበቅም። ይሁንና በምዕራፍ ተከፋፍሎም ሊሠራ የሚችልበት ዕድል አለ። እስካሁን ድረስ ግን በዚህ ጊዜ ይከናወናል ተብሎ የተቀመጠ ዕቅድ የለም።

መንገዱ ሙሉ ለሙሉ ቤቶች ላይ ነው የሚያርፈው ያሉት ኢንጂነር ታከለ፤ በዚህ የተነሳ ብዙ ወጪ የሚጠይቁ የካሳ ክፍያ ጉዳዮችም መጠናቀቅ አለባቸው። የከተማ አስተዳደሩ ካለው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው የሚባሉ መንገዶችን ቅድሚያ ይሰጣል ብለዋል።

እስከሁን ከአዲሱ ገበያ የሚነሳው ቀሪው የቀለበት መንገድ ግንባታ በ2015 ዓ.ም ዕቅድ አልተያዘለትም ሲሉ ተናግረዋል።

መንገዱ በመዲናዋ ማስተር ፕላን ውስጥ ከተካተቱና ካልተገነቡ መንገዶች መካከል አንዱ ነው። በመሆኑም ወደፊት ሁኔታዎች ሲመቻቹ በቀጣይ ዕቅድ ተይዞለት መገንባቱ አይቀርም፤ በመሆኑም መቼ ይገነባል ብለው ለሚጠይቁ ሰዎች ይሄ ነው የሚባል መልስ መስጠት አይቻልም ሲሉ ሃሳባቸውን አቅርበዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለሰላም ስምምነቱ ስኬታማነት በመንግሥት የተወሰዱ ርምጃዎች ችግሮችን በራስ አቅም የመፍታት አቅምን አሳይተዋል!

ኢትዮጵያ የታሪክ ገናናነቷ ከሚገለጥባቸው ዕውዶች አንዱ በዘመናት ሂደት ውስጥ ያልተቆራረጠ ሥርዓተ መንግሥት አጽንታ መኖሯ ነው። ይሄ የሥርዓተ መንግሥት ዘላቂነት ከፈጠረላት አቅምና የህሳቤ ልዕልና አንዱ ደግሞ፤ ችግሮችን በራስ እሴት እና አቅም መፍታት ይቻላል የሚለው ነው። ይሄንኑ ህሳቤዋን እንደ ሀገር ብቻ ሳይሆን እንደ አህጉር አጽንታ የምታቀነቅን ሲሆን፤ አፍሪካ እንደ አህጉር በውስጧ የሚስተዋሉ ችግሮችን በራሷ አቅምና እሴት መፍታት ትችላለች ለሚለው ሃሰብም መነሻ ተደርጎ ይወሰዳል።

በዚህ ረገድ በአፍሪካ የሚስተዋሉ ግጭቶችና አለመረጋጋቶች ቀድመው የሚታዩ ጉዳዮች ሲሆኑ፤ አፍሪካ የግጭትና ያለመረጋጋት አለፍ ሲልም በመፈንቅለ መንግሥት የመታመሷ ምስጢር በውስጧ የሚታዩ ችግሮችን በራስ አቅም ከመፍታት ይልቅ ለውጪ ኃይሎች ዳኝነት ራሷን አሳልፋ በመስጠቷ ነው የሚሉ ብዙዎች ናቸው። ኢትዮጵያም ይሄን ስለምትገነዘብ እንደዚህ አይነት ችግሮች በዘላቂነት ይፈቱ ዘንድ በውስጥ አቅምና በዜጎች ይሁንታ ላይ ተመሥርቶ የሚከወን መፍትሔ ሊሰጠው ይገባል የሚል አቋምን ስታራምድ ኖራለች።

ይሄ ህሳቤ ደግሞ ከብሂል ባለፈ በተግባር የሚገለጥ ሊሆን ስለሚገባውም፣ ኢትዮጵያ በውስጧ ለሚስተዋሉ ችግሮችም ሆነ ድንበር ዘለል መስለው ለሚስተዋሉ ጉዳዮች በቅድሚያ ባለ ጉዳዮቹ ቁጭ ብለው እንዲመክሩ፤ አለፍ ሲልም የአፍሪካውያን ተቋም የሆነው የአፍሪካ ኅብረት ጉዳዩን በባለቤትነት እንዲመራውና ለመፍትሔ እንዲበቃ ስታደርግ ቆይታለች። ኢትዮጵያ አስቦና አቅዶ በራስ አቅም መሥራትና መበልጸግ፤ ይሄን ተከትሎ የሚስተዋሉ ችግሮች ቢኖሩ እንኳን ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ተቀራርበው በመነጋገር ችግሮቻቸውን ያለማንም የውጪ ኃይል ጣልቃ ገብነት መፍታት ይቻላል የሚል አቋሟን አደባባይ ያወጣችበት የዓባይ ኃይል ማመንጫ ግድብ ደግሞ የዚህ ህሳቤዋና አቋሟ ውጤታማነት አንዱ ማሳያ ነው።

ከዚህ በላይ ግን በሃገራዊ ለውጡ ዘመን በሃገር መከላከያ ሠራዊት ሰሜን ዕዝ ላይ የተፈፀመውን ጥቃት ተከትሎ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የተፈጠረው ጦርነት ሰላማዊ መቋጫ እንዲኖረው የተደረገበት አግባብ የኢትዮጵያን ህሳቤ አዋጭነት፣ ታላቅነትና ተጨባጭበት ያረጋገጠ ሐቅ ሆኗል። የሰሜኑ ጦርነት መቀስቀስን ተከትሎ ኢትዮጵያም ሆነች የአፍሪካ ኅብረት ይሄን የመፍታት አቅም እንደሌላቸው ተደርጎ በስፋት ሲነገር፤ ችግሩ ከኢትዮጵያም ሆነ ከአፍሪካ አቅም በላይ ስለሆነም ሌሎች ዓለምአቀፍ ተቋማትና ሃገራት ወደራሳቸው ወስደው እንዲያዩትም የበዛ ግፊት፣ ቅስቀሳና ጫናም ሲደረግ ቆይቷል።

ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ በውስጧ የተከሰቱ ችግሮችን በራስ አቅም መፍታት ይቻላል፤ ይሄ ባይሳካ እንኳን በአፍሪካ ውስጥ የሚስተዋሉ ችግሮች ከራሳቸው ከአፍሪካውያን አቅም በላይ አይደሉምና አፍሪካዊ መፍትሔ ይኖራቸዋል በሚለው አቋሟ ጸንታ ተጉዛለች። እናም ጉዳዩ በውስጥ የሰላም ፍላጎት ታግዞ እና በአፍሪካ ኅብረት ጥላ ስር ቁጭ ተብሎ እንዲፈታ በብርቱ ጥራለች። ጥረቷም ለፍሬ በቅቶ በአፍሪካ ምድር በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ ላይ የሰላም ስምምነት ፊርማን በማኖር መቋጫ አግኝቷል። በኋላም በናይሮቢው መድረክ ታግዞ ስምምነቱ የበለጠ ጸና። ጉዳዩንም ወደ ባለቤቷ ኢትዮጵያ ተመልሶ ችግሩ አለ በሚባልበት ስፍራ ላይ ያለማንም አመቻችነት በጋራ ቁጭ ብሎ መነጋገር እና መፍታት እንደሚቻል ዓለም እንዲማር የተደረገበት ውይይት ተካሂዷል።

ቀደም ሲል የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ የተወሰዱ ርምጃዎች፣ ማለትም፣ የሰብዓዊ ድጋፍ ያለገደብ እንዲገባ መደረጉ፤ የወደሙ መሠረተ ልማቶች እንዲጠገኑ እና ወደ አገልግሎት እንዲገቡ መሠራቱ፤ ይሄን ተከትሎም ስልክ፣ ባንክ፣ ኤሌክትሪክና ሌሎችም የተቋረጡ አገልግሎቶች ዳግም እንዲጀምሩ መደረጉ፤የአየር በረራዎች መጀመራቸው፤... የመንግሥትን የሰላም ስምምነቱን ለማጽናት ያለውን ከፍ ያለውን ከሰላም ስምምነቱም የላቀ ቁርጠኝነት ያረጋገጡ ተግባራት ነበሩ።

በአጠቃላይ የሰላም ስምምነቱን ለማጽናት በመንግሥት በኩል የተወሰዱ በርካታ ርምጃዎች ኢትዮጵያ ችግሮቿን በራሷ አቅም መፍታት እንደምትችል ስትናገር የነበረውን እውነት ለዓለም የገለጠችበት፤ ኢትዮጵያም ሆነች አፍሪካ ችግሮችን በራስ አቅም መፍታት እንደሚችሉ ያረጋገጡ ነበሩ። ለሁለት ዓመታት የዘለቀውን ጦርነት ወደ ሰላም በመለወጥም ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚከሰቱ ችግሮች ሁሉ መፍትሔው ያለው በኢትዮጵያውያን እጅ መሆኑን አሳይታለች።

ከሰላም ስምምነቱ ማግስት ያለው አጠቃላይ ጉዞ ሲታይ የተወሰዱ ርምጃዎች እና ተጨባጭ ተግባራት የመንግሥትን የሰላም ቁርጠኝነት ያረጋገጡ መሆኑን አሳይቷል። ኢትዮጵያም የውስጥ ችግሮቿን በራሷ አቅም መፍታት እንደምትችል ለዓለም ማሳየት ችላለች!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## መልካም አጋጣሚዎችን ለቱሪዝም ማነቃቂያ መጠቀም ይገባል!

ፒያንኪ ዘኢትዮጵያ

ባለፉት ጥቂት ዓመታት በኮሮና ቫይረስ (COVID-19) ወረርሽኝ እና በሰላም እጦት ምክንያት ብርቱ ፈተና ገጥሞት የቆየው የኢትዮጵያ የቱሪዝም ዘርፍ፣ ባጋጠሙት ፈተናዎች ምክንያት ለአገራዊ ምጣኔ ሀብት የሚያበረክተው አስተዋፅዖ በእጅጉ ተቀዛቅዞ ቆይቷል። ከወረርሽኙና በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ከተፈጠሩት የሰላም መደፍረሶች፣ በተለይ ደግሞ በሰሜን ኢትዮጵያ ከተከሰተው ጦርነት፣ በፊት ዘርፉ በጥቅል አገራዊ ምጣኔ ሀብት ላይ የነበረው ሚና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቶ ነበር። በስራ እድል ፈጠራና በውጭ ምንዛሬ ግኝት አገራዊ ምጣኔ ሀብቱን የሚደግፈው ይህ ዘርፍ፣ አገሪቱ በዘርፉ ካላት አቅም አንፃር በአገራዊ ምጣኔ ሀብቱ ላይ ያለው ሚና የሚፈለገውን ያህል ባይሆንም እድገቱ መሻሻል ዕያሳየ እንደነበር አይዘነጋም።

የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ የጎብኚዎችን እንቅስቃሴ በመገደብ፣ በቱሪዝም ዘርፍ የተሰማሩ ተቋማትንና ግለሰቦችን ከስራ ውጭ በማድረግ ዓይነት ብዙ ግለሰባዊና ተቋማዊ ምስቅልቅሎች እንዲፈጠሩ አድርጓል። ኮቪድ-19 ወደ ኢትዮጵያ ከገባ ከጥቂት ወራት በኋላ የሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ 98 በመቶ ኪሳራ ውስጥ መግባቱን የኢትዮጵያ ሆቴል ባለሙያዎች ማኅበር መግለጹ የሚታወስ ነው። ይህንን ተከትሎም ሆቴሎች የቀጠሯቸውን ሠራተኞች ከሥራ እስከማሠናበት ደርሰው ነበር። ለወትሮው በጎብኚዎች የሚጨናነቁት አንዳንድ አካባቢዎች «ኧረ የጎብኚ ያለህ!» ብለዋል። የቱሪዝም ዘርፉ በወረርሽኙ እየተፈተነ በነበረበት ወቅት የተከሰቱት ግጭቶች (በተለይም የሰሜን ኢትዮጵያው ጦርነት) ደግሞ የዘርፉን ችግር በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ አድርገውበታል።

በኢትዮጵያ በቱሪስት መስህብነት ከሚያገለግሉ ሀብቶች መካከል ታሪክ፣ ባህልና ተፈጥሮ በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳሉ። በታሪክ ረገድ ላቅ ያለ የቱሪስት መነኻሪያ የሆነው የሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በጦርነቱ ምክንያት ያጋጠሙት ፈተናዎች በቱሪዝም ዘርፉ ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድረዋል። ጦርነቱ የቱሪዝም እንቅስቃሴው እንዲቋረጥ ከማድረጉ በተጨማሪ፣ የቱሪዝም መዳረሻዎችና አገልግሎት ሰጭ ተቋማት እንዲወድሙም ምክንያት ሆኗል። በጦርነቱ የሃይማኖት ተቋማትን ጨምሮ፣ በርካታ የቱሪዝም አገልግሎት መስጫ ተቋማት፣ ሙዚየሞችና ሌሎች የታሪክና የባህል ሀብቶች ወድመዋል፤ ተዘርፈዋል። ወረርሽኙም ሆነ ጦርነቱ የውጭ አገራት ጎብኚዎች ወደ ኢትዮጵያ እንዳይመጡ እንቅፋት ከመሆናቸው በተጨማሪ የአገር ውስጥ ጎብኚዎች እንቅስቃሴም ገትተዋል። ጦርነቱ የቱሪዝም እንቅስቃሴው እንዲቋረጥ በማድረግ ከዘርፉ ይገኝ የነበረውን የውጭ ምንዛሬ ከማሳጣቱ በተጨማሪ፣ ኑሯቸውን በቱሪዝም መዳረሻ አካባቢዎች አድርገው በቱሪዝም ዘርፍ የሚተዳደሩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ለከፍተኛ ችግር እንዲጋለጡም አድርጓል።

በኮሮና ቫይረስ እና በሰላም እጦት ችግሮች ከፉኛ ተፈትኖ የቆየው የኢትዮጵያ የቱሪዝም ዘርፍ በአሁኑ ወቅት ካጋጠሙት ፈተናዎች ለመውጣት በትልቅ ትግል ላይ ይገኛል። ከሁለት/ሦስት ዓመታት በፊት ከነበረው ነባራዊ ሁኔታ ጋር ሲነፃፀር አሁን በተሻለና ቀለል ባለ ሁኔታ ላይ የሚገኘው የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ የቱሪዝም ዘርፉ ተመልሶ እንዲነቃቃ እድል የሚፈጥር እንደሆነ ይገለፃል። በእርግጥ ቀደም ሲል የጎብኚዎችን ዝውውር በእጅጉ የጎዳው የወረርሽኙ መስፋፋት በአሁኑ ወቅት ያሳየው መቀነስ፣ የጎብኚዎችን ዝውውር በማነቃቃት የቱሪዝም ዘርፉ እንቅስቃሴ ቀስ በቀስ ቀድሞ ወደነበረበት እንዲመለስ እድል መፍጠሩ አይቀርም። የኢትዮጵያ የቱሪዝም ዘርፍም የዚሁ እድል ተጠቃሚ እንደሚሆን ይጠበቃል።

ሌላው ለኢትዮጵያ የቱሪዝም ዘርፍ መነቃቃት እድል እንደሚፈጥር የሚጠበቀው በዘርፉ ላይ ከፍተኛ ጉዳት አስከትሎ ለነበረው ለሰሜን ኢትዮጵያው ጦርነት መቋጫ ይሆን ዘንድ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ መንግሥትና በህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት) መካከል የተፈረመው የሰላም ስምምነት ነው። ስምምነቱ ሰላም እንዲሰፍን በማድረግ አጠቃላይ የዘርፉ እንቅስቃሴ እንዲሻሻል ከፍተኛ የሆነ በጎ አስተዋፅዖ ይኖረዋል። ስምምነቱ ጦርነቱ በአገር ገፅታ ግንባታ ረገድ ፈጥሮት የነበረውን በጎ ያልሆነ መልክ በመቀየር ጎብኚዎች ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ መበረታታትን ይፈጥራል። በዚህም የቱሪስቶች ፍሰት እንዲጨምርና ቆይታቸው ሰላማዊና የተራዘመ እንዲሆን በማድረግ ከዘርፉ የሚገኘው ገቢ እንዲጨምር ያስችላል።

የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ የቱሪዝም ዘርፉ መነቃቃትን እያሳየ እንደሆነ የቱሪዝም ሚኒስቴር አስታውቋል። ከስምምነቱ መፈረም በኋላ ለጉብኝትና ለስራ ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ የውጭ አገራት ዜጎችና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ዳያስፖራዎች ቁጥር እየጨመረ መሆኑን የገለፀው ሚኒስቴሩ፣ ይህ ሁኔታ በቀጣዮቹ ጊዜያትም እንደሚቀጥል ጠቁሟል። ይህ መረጃ የሚያመለክተው የሰላም ስምምነቱ ትሩፋቶች ገና በጠዋቱ ለቱሪዝም ዘርፉ መነቃቃት በጎ አስተዋፅዖ ማበርከት መጀመራቸውን ነው።

የሰላም ስምምነቱ የቱሪዝም ዘርፉ በጊዜያዊነት እንዲነቃቃ ከማስቻሉም በላይ ዘላቂ የሆነ እድገት እንዲኖረውም ያግዛል። ቱሪዝም ሰላምን በእጅጉ የሚሻ ዘርፍ በመሆኑ ስምምነቱ ሰላምን በማስፈን የቱሪስቶች ፍሰት በቋሚነት እንዲጨምር እንዲሁም በጦርነቱ የወደሙ የቱሪዝም ተቋማት መልሰው እንዲገነቡ በማድረግ የቱሪዝም ዘርፉ መነቃቃትና እድገት ቋሚ/ዘላቂ እንዲሆን ያስችላል።

ሰሞነኛ ሁኔታዎችም ለቱሪዝሙ ዘርፍ መነቃቃት እድል የሚፈጥሩ ተጨማሪ መልካም አጋጣሚዎች ናቸው። በተለይ በጥር ወር በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች የሚከናወኑ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ኹነቶች የዚህ መልካም አጋጣሚ ዋነኛ ማሳያዎች ናቸው። ደማቅ በሆነ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ስርዓቶች የሚከወኑት እነዚህ በዓላትና ጨዋታዎች የጎብኚዎችን ቀልብ የሚስቡና ለብዙ ዜጎች የስራ እድሎችን በመፍጠር ገቢ የሚያስገኙ እንደሆኑ ይታወቃል። ከእነዚህም መካከል በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ተቋም (ዩኔስኮ) የተመዘገበው የጥምቀት በዓል ዋነኛው ተጠቃሽ ነው። በዓሉ በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች በድምቀት የሚከበር ኃይማኖታዊ ክዋኔ ከመሆኑ ባሻገር በበዓሉ ላይ የሚስተናገዱት ልዩ ልዩ ባህላዊ ጨዋታዎች የበዓሉን ድምቀት ከፍ የሚያደርጉ ተጨማሪ ቅመሞች ናቸው። እነዚህ ጨዋታዎች የጎብኚዎችን ቀልብ በመሳብ ረገድ ትልቅ ሚና አላቸው። ስለዚህ እነዚህን ሰሞነኛ ክዋኔዎች በስፋት በማስተዋወቅና ባህልና ስርዓቱን በጠበቀ መልኩ በማከናወን የቱሪዝሙ ዘርፍ እንዲነቃቃ ማድረግ ይገባል። በአጠቃላይ ወቅታዊ ሁኔታዎች (የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ መቀነስ፣ የሰላም ስምምነቱ፣ ሰሞነኛ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ክዋኔዎች...) የፈጠሯቸውን መልካም አጋጣሚዎች በሚገባ በመጠቀም በተደራራቢ ፈተናዎች የተጎዳውን የቱሪዝሙን ዘርፍ ማነቃቃት ይገባል።

በተደራራቢ ችግሮች ምክንያት ዘርፈ ብዙ ፈተናዎች የገጠሙት የኢትዮጵያ ቱሪዝም ከገጠመው ችግር እንዲወጣ አስቸኳይ የማገገሚያ ሥራዎችን ማከናወን ያስፈልጋል። ከዚህ አንፃር ጉዳት ያስተናገደውን ማኅበረሰብ በማነቃቃት የማኅበረሰቡ እንቅስቃሴ በፍጥነት እንዲያገግም ማድረግ፣ የወደሙ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን መልሶ ማልማት፣ የአገር ውስጥ ቱሪዝምን ማበረታታት፣ በቀጣይም የቱሪዝም ዘርፉ የኢንሹራንስ አገልግሎት እንዲኖረው ማድረግ... ይገባል።

# ነፃ ሃሳብ

## የዳቦ ቅርጫት የመሆን ጡቦች

ዘካርያስ ዶቢ

የስንዴ ልማቱን፣ የበርካታ ግዙፍ ዳቦ ቤቶች ግንባታን ዜናን ስሰማ የዘመነ ደርግ የመጀመሪያዎቹ ዓመታት አንድ ዜማ ታወሰኝ። ዜማው ያኔ ይውጣ እንጂ ከዚያም በኋላ ተዜሟል። ዜማው ‹‹ሀ..ሁ ኢትዮጵያ ትቅደም...›› የሚል ነው። በዚህ ዜማ ውስጥ የሚገኙት ‹‹...ተብላ እንዳልነበር የዳቦ ቅርጫት፣ እንዴት እናታችን ትባል ራባት...›› የሚሉት ስንኞች የቁጭት መልእክት የሚያስተላልፉ ናቸው። ወቅቱ የ66ቱ ድርቅ ያስከተለው ረሀብ በርካታ ኢትዮጵያውያንን ፈጅቶ፣ ከቀዬቸው አፈናቅሎ፣ ለተረጂነት ዳርጎ ስለነበር የዳቦ ቅርጫት በመባል ትታወቅ የነበረችውን አገር ገጽታም በእጅጉ አበላሽቷል።

ድርቁ የ1966ቱን የንጉሱን አገዛዝ አሻፈረኝ ያሉ ወገኖች አመጽ ይበልጥ እንዲቀጣጠል ምክንያት ሆኗልም ይባላል፤ የአገሪቱን ገጽታም በእጅጉ አበላሽቶታል። የዳቦ ቅርጫቷን አገር የእንግሊዝኛው መዝገበ ቃላት የረሀብ ማሳያ ያደረጋትም ከዚያ ዘመን የሚጀመር ይመስለኛል። መዝገበ ቃሉ ድርቁን ‹‹ፋሚን›› ካለው በሁዋላ ስለፋሚን ማብራሪያ ሲሰጥ ምሳሌ የጠቀሰው ኢትዮጵያን ነው። ከዚያ ወዲህም እንደ 77ቱ ያሉ የድርቅ ወቅቶች በአገሪቱ ተከስተዋል። ሁሉም የአገሪቱን ገጽታ በእጅጉ እንዲጎድፍ አርገዋል።

በዚህች አገር ያን ገጽታ ለመቀየር ከ1966 ዓ.ም ወዲህ የመጡ መንግስታት ሁሉ ብዙ ጥረቶች አድርገዋል፤ ደርግ በ1977 ዓ.ም በአገሪቱ የተከሰተውን አስከፊ ድርቅ ተከትሎ እርዳታ ከማቅረብ በተጨማሪ ዘላቂ መፍትሄ ያለውን እርምጃ ወስዷል። አንዳንድ ወገኖች ሰፈራውን ሌላ ፖለቲካዊ መልክ ሊያላብሱት ቢሞክሩም፣ ለምነታቸው በተሟጠጡና ለድርቅ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች የሚኖሩ ዜጎችን ወደ ለም አካባቢዎች አስፍሯል። በዚህም የበርካታ ዜጎችን የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ ተችሏል፤ አንዳንዶችም ወደ ሀብት ማማ ወጥተውበታል።

በዚያ ዘመን በተካሄደው ሰፈራ ውጤት መታየቱንና ይህም የወቅቱ መንግስት ስኬት ተደርጎ መወሰዱን የሚያመለክት የሙዚቃ ድርሰት ጭንር በወቅቱ ወጥቶ ነበር። ይህ ሙዚቃ ታዋቂ አርቲስቶች ጭምር የተካተቱበት ነበር። ከእነዚህ መካከል አንዱ ድርሰት ‹‹የብሩህ ተስፋ እሸት›› ይሰኛል።

የብሩህ ተስፋ እሸት ካሴት በጊዜው በነበረው የኢትዮጵያ ሙዚቀኞች ማህበር አስተባባሪነት ገቢው በድርቅ የተጎዱ ወገኖችን ለመርዳት ተብሎ መዘጋጀቱን መረጃዎች ያመለክታሉ። ዝነኞቹ የሮሃና ዋልያስ ባንዶች እና በ12 ድምጻውያን የተዘጋጀ ነበር። ከድምጻውያኑ ስድስቱ ከአንጋፋ (አልዲስ) ስድስቱ ደግሞ በወቅቱ ያቆጠቆጡ፣ የጎመሩ ወጣት ድምፃውያን ነበሩ። የብሩህ ተስፋ አሸት ሕብረ- ዝማሬ ግሩም እንደነበረም ነው የሚገለጸው። በዚህ ዜማ፡-

የብሩህ ተስፋ እሸት አፈራ ጎመራ፤

በመላ ኢትዮጵያ ብሩህ ተስፋ ዘራ፤ ...

የሚሉት ስንኞች የሚያመለክቱትም በወቅቱ በተወሰደው ርምጃ በግብርናው ዘርፍ ለውጥ መምጣቱን የሚያመለክቱ ናቸው። በዚሁ ዘመን የ‹‹አረንጓዴ ዘመቻ››ም ተካሂዶ እንደነበር ይታወሳል። ለምሳሌ፣ ኢህአዴግ አገሪቱን ማስተዳደር ከጀመረ በኋላ እንዳልነበር የሆነው የፓዊ የበለስ የመስኖ ልማት ያኔ በግብርናው ዘርፍ በተለይም ድርቅ እያስከተለ ከነበረው ችግር ለመውጣት ሲከናወን ለነበረው ተግባር ጥሩ ማሳያ ነው። በወቅቱ በቴሌቪዥን ይተላለፉ የነበሩ የፓዊ የመስኖ እርሻን የተመለከቱ ዘገባዎች አሁንም ድረስ ይታወሱኛል። በኛ አገር እየተፈጸመ ያለ አይመስልም ነበር። ኢህአዴግ እሱን ሰብሮ ጣለው።

በተመሳሳይ የጋምቤላው አልዌሮ ግድብ ተቀደመ እንጂ ደርግ ሌላው ታምር ሊሰራበት የታቀደ እንደነበርም ይገለጻል። እንዲህ እንደ ዛሬው ብዙ የተባለላቸው በርካታ ዳቦ ቤቶች በአዲስ አበባ ተገንብተውም ነበር። ምንም እንኳን በኢህአዴግ እድሜ እንዲኖራቸው ባይደረግም ሁሉም ጥረቶች ያን የዳቦ ቅርጫትነት ዘመን ለመመለስ የተሞካከሩ ስራዎች ይመስሉኛል።

በኢህአዴግ ዘመንም ቢሆን ግብርናው ላይ ለመስራት ጥረት ተደርጓል። ግብርና መር የኢኮኖሚ ፖሊሲ ተግባራዊ በማድረግ ለውጦች ማሳየት ተችሏል። በእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዶቹም ግብርናው ላይ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣትና በኢኮኖሚው ያለውን ድርሻ ወደ ኢንዱስትሪው ለማዞር ተሞክሯል። ይሁንና ካለው የግብርና ምርት ፍላጎት አኳያ ሲታይ ግብርናው ገና ብዙ ይቀረው ነበር። ታዩ የሚባሉ ለውጦችም ግብርናው ይፈልግ ከነበረው መዋቅራዊ ለውጥ አንጻር የሚጠበቀውን ውጤት ያመጡ አልነበሩም።

> ጠቅላይ ሚኒስትሩ በቀጣይም በሀዋሳ፣ በጎንደር፣ በሐረር፣ በቦንጋ እና በሌሎች ዋና ዋና ከተሞች የዳቦ ፋብሪካዎች ይመረቃሉ ሲሉ ጠቅሰው፣ ይህም ኢትዮጵያን የዳቦ ቅርጫት የማድረግ የመጀመሪያው ጡብ የተቀመጠበት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል ብለው ነበር፡፡

ከ2010ሩ አገራዊ ለውጡ በኋላ በግብርናው ላይ በትኩረት እየተሰራ ነው። ግብርናው ዘርፍ ላይ ምርትና ምርታማነት እየታየ መሆኑ ታምኖበት፣ አድናቆት ተችሮትም ነበር፤ ይሁንና እንደ አገር ካለው የግብርና ምርት ፍላጎት እየጨመረ መምጣት አንጻር ሲታይ እድገቱ እዚህ ግባ የሚባል ሊሆን አልቻለም። እናም ዘርፉ ካለው እምቅ አቅም አኳያ እንዲሁም ከአቅርቦት ፍላጎት ክፍተቱ አኳያ ሲታይ በእርግጥም ዘርፉ ትልቅ ሪፎርም የሚያስፈልገው ሆኖ ተገኝቷል።

በመሆኑም መንግስት በግብርና ላይ ትኩረት አድርጎ የመስራት አስፈላጊነትን በማመን ወደ ስራ ገብቷል። ባለፉት አራት ዓመታት በግብርናው ዘርፍ በተለይ በስንዴ ልማት ላይ እየታየ ያለው ለውጥም ይህን ተከትሎ የመጣ ነው። በአጠቃላይ በግብርናው ምርትና ምርታማነት ላይ ለውጥ ለማምጣት እየተሰራ ሲሆን፣ በስንዴ፣ በሩዝና በአንዳንድ የእህል አይነቶች ምርትና ምርታማነት ላይ ለውጦች እየታዩ ናቸው።

በተለይ በስንዴ ልማቱ ላይ የታየው እምርታ ዓለምን ጭምር አስደምሟል፤ ያለፈው ዓመት የብሉንበርግ፣ የኬንያው ኔሽን ጋዜጣ ዘገባዎች፣ የአፍሪካ ልማት ባንክ ፕሬዚዳንት አድናቆት፣ ወዘተ የሚያመለክቱትም ይህንኑ ነው። በአገሪቱ ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ስንዴ በመስኖ እየለማ ነው። በዚህም ባለፈው ዓመት 26 ሚሊየን ኩንታል ስንዴ ተገኝቷል፤ ዘንድሮ ደግሞ 52 ሚሊየን ለማግኘት እየተሰራ ነው። በቆላማ አካባቢዎች የተጀመረው የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት አሁንም በሁሉም አየር ንብረቶች ላይ እየተካሄደ ይገኛል።

በስንዴ ልማቱ በመስኖ ላይ ብቻ አይደለም የተተኮረው፤ በመኸር ስንዴ ልማትም ላይ ትኩረት ተደርጎ እየተሰራ ነው። በመኸር ወቅት በስንዴ ዘር የሚሸፈነው ማሳ እየጨመረ ይገኛል። በቅርቡ የወጣ የግብርና ትራንስፎርሜሽን መረጃ እንደሚያመለክተው፤ አገሪቱ በሁለቱም መንገዶች ከ107 ሚሊየን ኩንታል በላይ ስንዴ ለማምረት እየሰራች ትገኛለች።

በዚህም በስንዴ ልማቱ የአገር ውስጥ ፍላጎትን ሙሉ ለሙሉ ከመመለስ በተጨማሪ፤ ሌሎች ታሳቢ የተደረጉ ስራዎችም አሉ። ስንዴ ለጎረቤት አገሮች ገበያ ማቅረብ እና የውጭ ምንዛሬ ማግኘት የሚሉት፤ እነዚህን ለማሳካትም ነው እየተሰራ ያለው።

ይህን ተከትሎም የጎረቤት አገሮች ፍላጎት እያሳዩ ይገኛሉ። የአገር ውስጥ የስንዴ ፍላጎት 90 ሚሊየን ኩንታል እንደሆነ መረጃዎች ያመለክታሉ። ይገኛል ተብሎ ከሚታሰበው በላይ የሚሆነውን የስንዴ ምርት ነው ለውጭ ገበያ ለማቅረብ የታቀደው። የስንዴ ልማቱ ፖለቲካዊ ፋይዳም አለው። በስንዴ እርዳታ ሊሸነግሉን ለሚፈልጉ አካላት ግልጽ መልእክት የተላለፈበት ዋና ተግባርም ነው። ይህ ትልቅ እምርታ ነው።

በእርግጥም የአገር ውስጥ የስንዴ ፍላጎትን ሸፍኖ ለውጭ ገበያ መድረስ ትልቅ እምርታ ነው። የስንዴ እርዳታ ይደረግላት እና ስንዴ ከውጭ ስትገዛ የነበረች አገር ከውጭ ስንዴ ማስገባቷን ማስቀረቷ፣ የራሷን ፍላጎት አሟልታ ለውጭ ገበያ ማቅረቧና የውጭ ምንዛሬ ማግኘት ማቀዷ ልማቱ ምን ያህል እምርታ እንደታየበት መረዳት አያዳግትም።

አገሪቱ ስንዴ በማምረት ብቻ አልተገታችም። በዳቦ ፋብሪካዎች ግንባታም ተጠምዳለች። የሸገር ዳቦ ፋብሪካ በአዲስ አበባ የተለያዩ አካባቢዎችና በከተማዋ ዙሪያ በሚገኙት የኦሮሚያ ከተሞች ዳቦ ለማቅረብ እንደሚሰራ ይገልጽ ነበር፤ በከተማዋ አቅራቢያ በሚገኙት ከተሞች ስላለው ሁኔታ ባላውቅም፣ ለአዲስ አበባ ዳቦ እያቀረበ ነው፤ በእዚሁ በአዲስ አበባ በቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸው ፕሮጀክት ሌላ የዳቦ ፋብሪካ ተገንብቶ ተመርቋል። የቀዳማዊ እመቤቷ ፕሮጀክቶች ዳቦ ቤቶችን በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች እያስገነባ ይገኛል። በቅርቡም በወላይታ ሶዶና እና ሀዋሳ ከተሞች እያንዳንዳቸው በቀን 300 ሺ ዳቦዎችን የሚያመርቱ ፋብሪካዎች በቀዳማዊት እመቤቷ ፕሮጀክት ተገንብተው በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ተመርቀዋል።

የሸገር ዳቦ ፋብሪካ፣ በዚህ ላይ በእያንዳንዱ ክፍለ ከተማ በ90 ቀናት እቅድ ሁለት ሁለት ዳቦ ቤቶች እንደተገነቡ ስለመሆኑም እየተነገረ ነው፤ ዳቦ መጋገሪያ ህንጻዎቹ ቀጣይ ስራቸው ዳቦ መጋገሪያ ማሽኖች ተገጥሞላቸው ዳቦ መጋገርና በተመጣጣኝ ዋጋ ማከፋፈል ይሆናል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በወላይታ ሶዶ የተገነባውን በቀን 300 ሺ ዳቦዎችን የሚጋገርበትን የዳቦ ፋብሪካ በመረቁበት ወቅት እንዳሉት፤ የዛሬ አራት ዓመት አዲስ አበባ ውስጥ 300 ሺ ዳቦ አይጋገርም ነበር፤ ዳቦ መጋገሪያዎቹ ሁሉ ተደምረው ይህን ያህል ዳቦ አያመርቱም ነበር። ዛሬ አዲስ አበባ ውስጥ በሚሊየን የሚቆጠር ዳቦ በቀን እየተመረተ ነው። በአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን በዋና ዋና ከተሞችም ሰፋ ያለ ዳቦ የሚያምርቱ ፋብሪካዎች ኢትዮጵያ ይኑራት ተብሎ በተለያዩ ከተሞች ዳቦ ፋብሪካዎች ተገንብተው ይመረቃሉ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በቀጣይም በሀዋሳ፣ በጎንደር፣ በሐረር፣ በቦንጋ እና በሌሎች ዋና ዋና ከተሞች የዳቦ ፋብሪካዎች ይመረቃሉ ሲሉ ጠቅሰው፣ ይህም ኢትዮጵያን የዳቦ ቅርጫት የማድረግ የመጀመሪያው ጡብ የተቀመጠበት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል ብለው ነበር።

ይሄ ትልቅ ራእይ ነው። አገራችን የዳቦ ቅርጫት እንደነበረች የደርግ መንግስት ወደ ስልጣን በመጣበት ወቅት ይገልጽ ነበር። ‹‹ሀ..ሁ ኢትዮጵያ ትቅደም...›› በሚለው የወቅቱ ዜማ ውስጥ ከሚገኙት ‹‹ ተብላ እንዳልነበር የዳቦ ቅርጫት፤ እንዴት እናታችን ትባል ራባት›› ከሚሉት ስንኞች መረዳት የሚቻለውም ይህንን ነው። ይሁንና ከዚህ ይልቅ አገራችን የምትታወቀው አስከፊ በሚባሉ የድርቅ ክስተቶቿ ነው።

አሁን ግን ከስንዴ ልማቱ ውጤታማነት በተጓዳኝ፣ በአገሪቱ የተለያዩ ከተሞች ግዙፍ ዳቦ ቤቶች ለመገንባት መንግስት እና የቀዳማዊ እመቤት ፕሮጀክት እያደረጉ ካሉት ጥረት አኳያ ሲታይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉትም የዳቦ ቅርጫትነቷን እውን ማድረግ ይቻላል። ምክንያቱም እንደሚታወቀው የዳቦ ቤቶች መሰረታዊ ችግር ሆኖ የቆየው የስንዴ ችግር እየተፈታ ይገኛል። የዳቦ ጉዳይ ከዳቦ ቤቶች ወደ ዳቦ ፋብሪካዎች እየተሸጋገረ ነው። አሁን የሚጠበቀው ዳቦው ነው፤ ይህ ሲሆን አገሪቱ ወደ ዳቦ ቅርጫትነቷ እውን መሆን ምልክቶች ይበልጥ መታየት ይጀምራሉ።

አሁን ባለው ሁኔታ ሸገር ዳቦ ፋብሪካ እንደተባለለት ባይሆንም የዳቦ አቅርቦቱን ቀጥሎበታል። ሸገር ግዙፍ የዳቦ ፋብሪካ ነው፤ ከሚታይበት የአቅርቦት ወጣ ገባነት፣ ካለው የህብረተሰቡ ፍላጎት አኳያ ሲታይ ግን በሙሉ አቅሙ እያመረተ ነው ማለት ግን ያስቸግራል። በቀዳማዊ እመቤት ፕሮጀክት የተገነባው የዳቦ ፋብሪካ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራበት የሚገባ ስለመሆኑ ጠቋሚ ጉዳዮች አሉ። በ90 ቀናት እቅዱ የተገነቡት የዳቦ ቤቶች ህንጻዎች አስፈላጊዎቹ መጋገሪያዎች ተተክሎላቸው፣ የኤሌክትሪክ ኃይል ተዘርግቶላቸው ዳቦ ጋግሮ ወደ ማቅረብ መሸጋገር እንዲችሉ ተገቢውን ትኩረት እና እገዛ ሊደረግ ያስፈልጋል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት የግል ባለሃብቱን ወደዚህ ስራ እንዲገባ መደገፍና ማበረታታቱ ሲሆን፤ በዚህ ረገድ በቀደሙት የግል ዳቦ መጋገሪያዎች የሚስተዋሉ የዳቦ ግራም ጉዳይም መፈታት ይኖርበታል። በግራም በኩል ሸገር ጥሩ ነው። ሌሎቹም ዳቦ አይደለም እየሸጡ ያሉት፤ የዳቦ ቅርፊት ነው እየሸጡ ያሉት። ዋጋው ሰማይ እንደ ወጣ ነው፤ በግራሙ የተሻለ ዳቦ የሚያቀርቡት ዋጋም ተመላልሶ የሚያስገዛ አይደለም።

ዳቦ በሁሉም የማህበረሰብ ክፍል የሚፈለግ እንደመሆኑ ሸገርን ጨምሮ ሁሉም አዳዲስ ዳቦ ቤቶች ሁሉንም ማህበረሰብ ያማከለ የዳቦ አቅርቦት ላይ አተኩረው መስራት ይኖርባቸዋል። አዳዲስ ግዙፍ ዳቦ ቤቶች እየተገነቡ እንደመሆናቸው በአመጋገብ ላይም የባህል ለውጥ ይመጣል የሚል እምነት አለኝ፤ የእንጀራ አዘውታሪ የሆነው ህብረተሰብ የዳቦ አቅርቦቱ እየሰፋ ሲመጣ ዳቦ ተመጋቢ እንደሚሆን ይጠበቃል። ለሁሉም ግን ዳቦ ቤቶቹ ዳቦ ጋግረው ወደ ማቅረብ መሸጋገር፤ ከማሳ እስከ ጉርሻ ያለው ፍሰት ተሳልጦም የተጀመረውን ውጤት በማስቀጠል የዳቦ ቅርጫትነቱን ግስጋሴ እውን ማድረግ የሁሉንም ባለድርሻ ኃላፊነትን መወጣት ይጠይቃል። ሰላም !

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## ሌሎች ሳተላይቶችን ዲዛይን ለማድረግ መነቃቃት የፈጠረችው ሳተላይት

**ወርቅነሽ ደምሰው**

በዚህ ዘመን የሳተላይቶች ሚና በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ መጥቷል፤ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት፣ የአየር መንገድ እንቅስቃሴዎች፣ የአየር ጸባይ ለመረዳት የሚደረጉ ጥረቶች፣ የተለያዩ ወታደራዊና የሲቪል ስራዎች በሳተላይት የሚተላለፍ መረጃን ይፈልጋሉ። ቴሌቪዥኖችና ራዲዮኖች ሳተላይቶችን ይፈልጋሉ፤ ዛሬ አገልግሎቱ እየተስፋፋ የመጣው የጂፒኤስ ቴክኖሎጂም የሳተላይት መኖርን የግድ ይላል።

በአጠቃላይ ሳተላይቶች ለሀገሮች ምጣኔ ሀብት፣ ለወታደራዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች የተሳለጠ መሆን ያላቸው ሚና ከፍተኛ እየሆነ መምጣት፣ ሀገሮች ሳተላይቶችን ተከራይቶ ከመጠቀም ባሻገር የራሳቸውን ሳተላይት በማምጠቅ ስራ እንዲጠመዱ አድርጓቸዋል።

ሕዋ ላይ ያሉ ሳተላይቶች መረጃዎችን በመሰብሰብ ከግዙፍ ክንውኖች እስከ ጥቃቅን እንቅስቃሴዎች በመመዝገብ ይይዛሉ። ሳተላይቶቹ የመሬትና የሕዋ ሳይንስ ምልከታ፣ የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የከተማ ልማት፣ የአደጋን መከላከል ፣የካርታ ሥራ ፣ የግብርና የደን ልማት፣ የሜትሮሎጂ፣ የጂፒኤስ እና የዓለም አቀፍ የተፈጥሮ ሀብትን መቆጣጠር የሚያስችሉ መረጃዎችን በመስጠት ረገድ ያላቸው ጠቀሜታ ዘርፈ ብዙ ነው። ከዚህ ባሻገር የአየር ንብረት ለውጥን ለመቆጣጠር፣ የተፈጥሮ አደጋዎች ከመድረሳቸው አስቀድሞ ለመተንበይ፣ ደህንነትን ለመጠበቅ የሚረዱ መረጃዎችን ለማወቅ እንደሚውሉም መረጃዎች ያመላክታሉ።


በዓለም ላይ በፍጥነት እየዘመነ ያለውን የሕዋ ሳይንስ ዘርፍ በመጠቀም ያደጉት ሀገራት በተለያዩ ጊዜያት ሳተላይቶችን ወደ ሕዋ በማምጠቅ የመሬትና የሕዋ ምርምርን በማሳደግ ከዘርፉ ብዙ ጠቀሜታ አግኝተዋል። ለዚህም ነው ያደጉት ሀገራት ዓለምን ለመቆጣጠር የሚያስችል ሳተላይት በመገንባት ወደ ሕዋ በማስወንጨፍ ረገድ አንገት ለአንገት ተናንቀው እየተፎካከሩ የሚገኙት።

ኢትዮጵያም የሕዋ ሳይንስ ዘርፍን መቀላቀሏን ያበሰረችው በኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ባመጠቀችው Ethiopian Remote Sensing Satellite–01‹‹ETRSS-1›› የመሬት ምልከታ ሳተላይት አማካይነት ነው። ሳተላይቷ ታኅሣሥ 10 ቀን 2012 ዓ.ም ወደ ሕዋ መምጠቋ ይታወሳል። ሳተላይቷ ወደ ሕዋ ከመጠቀች ሦስተኛ ዓመቷን አስቆጥራለች። ወደ ሕዋ የመጠቀችው ለሁለት ዓመት ተኩል አገልግሎት እንድትሰጥ ታስባ ቢሆንም፣ የቆይታ ጊዜዋን በስድስት ወራት አራዝማ በመቆየቷ ሦስተኛ ዓመቷ በያዝነው የፈረንጆቹ ወር ተከብሯል።

በዛሬ ሳይንስና ቴክኖሎጂ አምዳችን ሳተላይቷ በእነዚህ ሦስት ዓመታት በሕዋ ላይ ስላከናወነቻቸው ተግባራትና ስለበረከተችው አስተዋጽኦ ዳሰናል።

የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስ እና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ አብዲሳ ይልማ እንደሚሉት ፤ ‹‹ETRSS -1›› የመሬት ምልከታ ሳተላይት የማምጠቁ ሂደት ለሁለት ዓመት ተኩል አገልግሎት እንድትሰጥ ታስቦ የተካሄደ ቢሆንም፤ ሳተላይቷ ተጨማሪ ስድስት ወራት በመቆየት አሁንም ድረስ መረጃ የመስጠት ተልዕኮዋን በአግባቡ እየተወጣች ነው። ይቺ ሳተላይት በኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስ ታሪክ የመጀመሪያዋ ስትሆን ወደ ሕዋ ከተላከች አንስቶም እጅግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያበረከተች ትገኛለች።

ሳተላይቷ በኢትዮጵያ ሕዋ ሳይንስ ላይ ስለፈጠረችው መነቃቃት፤ ስለሰጠችው መረጃ፤ ሳተላይትን ዲዛይን በማድረግ፣ በመፈተሽ፣ በመቆጣጠርና በመጠገን የቴክኖሎጂ አቅም በመፍጠር ረገድ ያበረከተችው አስተዋፅኦ ከፍተኛ መሆኑን አቶ አብዲሳ ጠቅሰው፤ ሳተላይትን ካመጠቁ አገራት ጎራ እንድንሰለፍ በማድረግ በገጽታ ግንባታ ላይ ስላደረገችው በጎ አስተዋፅኦም ተናግረዋል። በትውልዱ ላይ ስለጫረችው ተስፋና ስለፈጠረችው መነሳሳት እንዲሁም የ‹‹ETRSS-2›› የቅድመ ዝግጅት ሥራ እንዲከናወን መነሻና ብርታት መሆኗን አስታውቀዋል።



በሳተሳይቷ አማካይነት ከሦስት ሺ በሳይ የመረጃ ቅብብሉሽ ተደርጓል፡፡

የ ‹‹ETRSS -1››በኢትዮጵያ ስፔስ ፕሮግራም ውስጥ ለትውልድ የምትጠቀስ ታሪካዊ ሳተላይት ነች ያሉት አቶ አብዲሳ፤ ከሁሉ በላይ ደግሞ በሕዋ ውስጥ ከፍተኛ ሙቀትን እና ቅዝቃዜን እንዲሁም ከፀሐይ የሚነሱ አደገኛ ጨረሮችን፣ አለፍ ሲልም ‹‹ETRSS -1›› እኮ ጠፍታለች የሚሉ መርዶ ነጋሪዎችን የሟርት ቃላት ተቋቁማ የታቀደላትን የሁለት ዓመት ተኩል ጊዜ ማጠናቀቋ ሳያንስ ከተያዘላትም ጊዜ ስድስት ወር አሳልፋ እስካሁን ድረስ አገልግሎት እየሰጠች መሆኑን ነው ያብራሩት።

በሳተላይቷ አገልግሎት እጅግ ደስተኞች ነን ያሉት አቶ አብዲሳ፤ ለዚህ ከእንጦጦ ቁርና ብርድ ጋር እየታገሉ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ላበረከቱ የተቋሙ ሠራተኞች ምስጋና አቅርበዋል። ይህም ለተቋሙም ይሁን ለመላው ኢትዮጵያውያን ኩራት ያጎናጸፈ ትልቅ ገድል ነው ሲሉ ተናግረዋል።

የሳተላይት ኦፕሬሽን ዘርፉን የሚመሩት ኢንጂነር መላኩ ሙካ በበኩላቸው ኢትዮጵያ የመጀመሪያዋን የ‹‹ETRSS -1›› የመሬት ምልከታ ሳተላይት ወደ ሕዋ መላኳ በሀገር ገጽታ ግንባታ ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማበርከቱን ይናገራሉ። ኢትዮጵያ ሳተላይት ወደ ሕዋ ስታወናጭፍ በወቅቱ በሕዋ ላይ ያሉ ሳተላይቶች ወደ አርባ ይጠጉ እንደነበር ጠቅሰው፤ ኢትዮጵያ ከአፍሪካ አሥረኛ ሳተላይትን አወንጫፊ አገር መሆኗ በሕዋ ዘርፍ ስሟ ከፍ እንዲል ያደረገ ተግባር መሆኑን ነው ያብራሩት።

ሳተላይቷ ከመጠቀች ጊዜ ጀምሮ እስካሁን በርካታ ትሩፋቶችን እያስገኘች ነው ያሉት አቶ መላኩ፤ ይህም በዲዛይን፣ በጥገና እና በኦፕሬሽን ዘርፍ ያለውን የሰው ኃይል አቅም በመገንባት ለሌሎች የሚተርፍ ከፍተኛ አቅም መገንባት ያስቻለ አቅም መፍጠሯን እንደሚያመለክት ነው የገለጹት።

እንደ አቶ መላኩ ገለጻ፤ ሳተላይቷን ከመቆጣጠር እና ተልዕኮ ከመስጠት አኳያ በርካታ ሥራዎች ተሰርተዋል። በእነዚህ ሦስት ዓመታት ከሦስት ሺ በላይ የመረጃ ቅብብሎሽ የተደረገ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ከአንድ ሺ ሁለት መቶ በላይ የሚሆኑት ተልዕኮዎች ለሳተላይቷ ተሰጥተዋል። የውሃ ሀብትን አስመልክቶ መረጃ ለሚፈልጉ አካላት ተገቢው መረጃ ይሰጥ ነበር። በተለይም ከታላቁ ህዳሴ ግድብ ጋር ተያይዞ የሚፈለጉ መረጃዎችን ከመስጠት አንጻር ፤ በየዓመቱ የነበሩ የውሃ ሙሌቶችንና ከዚያ ጋር ተያይዞ የተገደበው ውሃ የሚይዘውን ቦታና የሚኖረውን ቅርጽ በ ‹‹ETRSS-1›› የመሬት ምልከታ ሳተላይት መረጃ ማወቅ አስችሏል።

ከዚህ በተጨማሪም የደን ሽፋንን፣ ለድርቅ እና ለጎርፍ ተጋላጭ የሆኑ የአፋርና የዳሰነች ቦታዎችን እንዲሁም የውሃ እጥረት ችግር ያለባቸውን አካባቢዎች መለየት ተችሏል። ሰፋፊ የፍራፍሬ ዛፎችን እና እርሻዎችን ደህንነት ለመቆጣጠርና ለመንከባከብ ከሳተላይቷ የሚገኘው መረጃ ጥቅም ይሰጥ እንደነበር ጠቅሰው፤ በዚህም በደቡብ ምዕራብ የኢትዮጵያ ስላለ የፍራፍሬ ጫካ እና በመተሃራ ሸንኮራ አገዳ ማሳ በተገኘው መረጃ ላይ ተመስርቶ ውጤታማ ሥራ መሥራት እንደሚያስችል ነው አቶ መላኩ ያብራሩት።

‹‹ኢትዮጵያ ሳተላይት ማስወንጨፏ ለአዲሱ ትውልድ መነቃቃትን ይፈጥራል፤ ይህንንም አጠናክራ መሄድ እንደምትችል ተስፋን የሚያሰንቅ ነው›› ያሉት አቶ መላኩ፤ በስፔስ ሳይንስ ዘርፍ ላይ እምነትና ተስፋ የሚጥል ትውልድ ለመፍጠር ያለው አስተዋፅኦ ከፍተኛ መሆኑንም ተናግረዋል። የነገ የሀገር ተረካቢ ወጣቶችና ተማሪዎች ከዩኒቨርሲቲዎች እና ከትምህርት ቤቶች እንጦጦ ኦብዘርቫቶሪ የምርምር ማዕከል መቆጣጠሪያ ጣቢያው ድረስ በአካል ተገኝተው በዘርፉ እየተሰሩ ያሉ ሥራዎች እንደሚጎበኙ ጠቅሰው፤ በጉብኝታቸውም በተመለከቱት እንደሚደነቁና በኢትዮጵያ በሕዋ ሳይንስ ዘርፍ የተጀመረው ሥራ እንዲህም ይቻላል እንዴ ብለው ነገን እንዲያስቡ፣ ተስፋ እንዲሰንቁ ያደረገ መሆኑን ነው አቶ መላኩ ያብራሩት።

ኢትዮጵያ ያስወነጨፈቻት የ«ETRSS -1» የመጀመሪያዋ ሳተላይት የመማሪያ መጻሕፍት ሽፋን እንዲሆን መደረጉንም ጠቁመዋል። በተጨማሪም የሕዋ ሳይንስ ትምህርት በአንድ ምዕራፍ በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ እንዲካተት መድረጉ በትውልዱ ላይ መነቃቃት በመፍጠር እንደሚያግዝ አመላክተዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ የ«ETRSS -1» ሌሎች ሳተላይቶች ዲዛይን ለማድረግ ትልቅ ራዕይ፣ ሞራልና መነቃቃት እንዲኖር ያደረገ ክስተት ነው። እንጦጦ ኦብዘርቫቶሪ የምርምር ማዕከል ከተለያዩ የዓለም ሳተላይቶች መረጃን በመቀበል ከብዙኃ ሳተላይቶች ጋር ቅንጅት በመፍጠር ሀገሪቷ የምትፈልገው የመረጃ ፍላጎት ተደራሽ እንዲሆን ያስቻለ አቅምን የፈጠረ ነው። ይህም የሀገሪቱ ተቋማትን ትልልቅ የመረጃ ፍላጎት ለመፍታት የ«ETRSS -1›› ቀጥሎ የተፈጠረው የብዝኃ ሳተላይቶች ዲዛይን አዲስ የፈጠራ ጥበብ የታየበት ነው። ይህ የብዝኃ ሳተላይቶች ዲዛይን በጣም ብዙ ሥራዎች የሚሰራ በዓለም ገበያ ውዱና በጣም ዘመናዊ የሚባል ሳተላይት ነው። ኢትዮጵያ እዚህ ላይ ቀድማ መድረሷ ደግሞ ትልቅ ስኬት ያስገኘ ነው።

የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ሁሪያ ዓሊ እንደተናገሩት፤ ዓለም ዛሬ የደረሰበት አራተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት ምዕራፍ የዲጅታል ቴክኖሎጂ፣ ሰው ሠራሽ አስተውሎት፣ አርተፊሻል ኢንተለጀንስ፣ የውሂብ አልተኔት ትንታኔ፣ የቁስ በይነ መረብ እና ሌሎች መጻኢ ቴክኖሎጂዎች ተዳምረው እንደኛ ሀገር በዕድገት ደረጃ ላይ ባሉ ሀገሮች ላይ ዕድልም ይዘው መጥተዋል፡፡ ፈተናም ጋርጠዋል፡፡

«አዲሱ የኢንዱስትሪ አብዮት ፈተና የሚሆንብን የኢንዱስትሪውን የለውጥ ሂደት እና አቅጣጫ በውል ሳንገነዘብ ለእሱ የሚመጥን የተግባር ሁሉን አቀፍ ዝግጅት ሳናደርግ ስንቀር ነው›› ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ በአንጻሩ ከተጠቀምንበት ከዚህ ቀደም የነበሩት የኢንዱስትሪ አብዮቶች ከከፈቱት እድል በላይ የግዴታ ከአንድ የኢንዱስትሪ ደረጃ ጠብቀን ወደ ሌላው ረድፍ መሄድ ሳይጠበቅብን ይልቁንም በዘግይቶ ደራሽ መልካም አጋጣሚ ተጠቅመን ፈጥነን መድረስ የሚያስችለን እድል የሚፈጥርልን ነው ይላሉ።

በተለይም 70 በመቶ የሚሆነው የሀገራችን ሕዝብ ወጣት በመሆኑ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ፣ የዲጂታል ቴክኖሎጂ ቱሩፋቶች ድንበር ሳይገደባቸው፤ ርቀት ሳይወስናቸው ከአንድ ዓለም ጫፍ እስከ ሌላው ዓለም ጫፍ ፈጥኖ መድረስ በሚቻልበት ዘመን አራተኛ የኢንዱስትሪ አብዮት ከፈተናዎቹ ይልቅ የመልማትና የማደግ እድል የሚፈጥሩበት አዝማሚያዎች በእጅጉ ልቀው እንደሚታይበት ነው ሚኒስትር ዴኤታዋ ያብራሩት።

በስፔስና የጂኦስፓሻል ዘርፍ እያስመዘገብናቸው ያሉ ውጤቶች አሁን ላይ የልማት ፕሮግራሞች ውጤታማነት ላይ የሚኖራቸው ፋይዳ እንደተጠበቀ ሆኖ የመጪው ጊዜ ተወዳዳሪነታችንን ከማጎልበት አኳያ የሚኖራቸው አብርክቶ ምትክ የለሽ መሆኑን የጠቆሙት ሚኒስትር ዴኤታዋ፣ ሦስት ዓመቱ የተከበረለት የመጀመሪያዋ የኢትዮጵያ የመሬት ምልከታ ሳተላይት የ«ETRSS -1›› አይን ገላጭ ሳተላይታችንን ከመሆኗም ባሻገር አስቀድሞ ከታሰበበት በተለይ ተጨማሪ ስድስት ወራት መቆየት መቻሏ ሁላችንን አስደስቷል ሲሉ ተናግረዋል።

# ወቅታዊ ትንታኔ

# የዋጋ ግሽበት መንስኤና መፍትሄው

**ምህረት ሞገስ**



**ሰው ወደ ገበያ ሔዶ የግብርና ምርቱን፤ ወተቱን፣ ስጋውንም፣ ስንዴውን ማግኘት ሲችል ዋጋው የሚረጋጋበት ሁኔታ ይኖራል**

በኅዳር ወር 2015 ዓ.ም ከምግብ ክፍሎች ውስጥ አትክልት ቅናሽ ቢያሳይም፤ በአብዛኛው እህሎች፣ ጥራጥሬ፣ የምግብ ዘይትና ቅባቶች፣ ሥጋና ወተት ጭማሪ በማሳየታቸው አጠቃላይ የምግብ ዋጋ ግሽበት እየቀጠለ እንደሚገኝ ከኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

ከምግብ በተጨማሪ ምግብ ነክ ያልሆኑ ልብስና ጫማ፣ ነዳጅና የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች ጭማሪ በማሳየታቸው በኅዳር ወር 2015 ዓመታዊ የዋጋ ግሽበት 35 ነጥብ 1 ከመቶ ተመዝግቧል። አጠቃላይ ደግሞ የዋጋ ግሽበቱ 31 ነጥብ 7 በመቶ መሆኑን ከኤጀንሲው ያገኘነው መረጃ ያሳያል። የዋጋ ግሽበቱ ዋነኛ ምክንያት እና መፍትሔውን በተመለከተ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ሙያዊ አስተያየታቸውን ሰጥተውናል።

ባለሙያዎቹ እንደሚሉት፤ የዋጋ ግሽበት በመሰረታዊነት ምክንያቱ የአቅርቦት እና የፍላጎት አለመጣጣም ነው። ይህ የሚከሰተው በብዛት ወደ ገበያው የተለቀቀው የገንዘብ መጠን እና ያለው ምርት ሳይመጣጠን ሲቀር ነው።

‹‹ብዙ ሰው ገንዘብ ይዞ ወደ ገበያ ሲሔድ የገንዘቡን ያህል ምርት ገበያው ውስጥ ከሌለ ብዙ ሸማቾች ለጥቂት ዕቃ የሚያደርጉት ውድድር የምርት ዋጋው ወደ ላይ እንዲወጣ ያስገድዳል›› የሚሉት የኢኮኖሚ ባለሙያው አቶ ወሰንሰገድ አሰፋ ናቸው። ሌላኛው ባለሙያ አቶ ዓለማየሁም ተፈሪም በዚሁ ሃሳብ ይስማማሉ።

እንደአቶ ወሰንሰገድ ገለፃ፤ ሽንኩርት፣ ቲማቲም እና መሰል የምግብ ሸቀጦች በገበያ ላይ በአንድ ኪሎ እስከ 70 ብር ድረስ ተሸጦ ነበር ፤ ሆኖም ግን መልሰው ብዙም ሳይቆዩ ዋጋቸው ወርዶ አንድ ኪሎ በ20 ብር ደርሷል። ይሔ የብሩ የመግዛት አቅም ጨምሮ ሳይሆን፤ ምርቱ ሲጨምር እና ያንን ምርት ለመግዛት ገበያ ላይ የሚውለው ገንዘብ ከምርቱ ጋር ተመጣጣኝ ሲሆን ዋጋው ስለቀነሰ ነው።

በተቃራኒው ምርቱ ሳይበዛ ምርቱን ለመግዛት የሚውለው ገንዘብ በጣም በብዛት ከታተመ እና ወደ ገበያ ከተበተነ፤ ገንዘቡ ስለበዛ ሽሚያ ይፈጠራል። ገንዘቡ ሲበዛ የሚመረተውም አብሮ ከበዛ ማለትም ዓመታዊ ምርቱ (ጂዲፒ) ገበያ ላይ ካለው ብር በታች ሳይሆን ተመጣጣኝ ከሆነ የዋጋ ግሽበት አይኖርም ሲሉ ያብራራሉ።

የገንዘብ ገበያው ላይ መበተን እንዴት እንደሚፈጠር የሚያስረዱት የኢኮኖሚ ባለሙያ አቶ ወሰንሰገድ እንደሚሉት፤ የኢንቨስትመንት መስፋፋት ጥቅም እንዳለው ሁሉ ጉዳትም አለው። ምክንያቱም መንግስትም ሆነ ባለሃብት ትኩረት አድርገው የሚሰሩባቸው ዘርፎች ህብረተሰቡ የሚሸምታቸው ወይም ወደ ውጭ ተልከው ገንዘብ የሚያስገኙ መሆን አለባቸው። ለምሳሌ አግሮ ኢንዱስትሪ ቢስፋፋ ህዝቡ ይሸምታል፤ ቤት ቢገነባ ህዝቡ ይኖርበታል፤ ነገር ግን ሰራተኛ ተቀጥሮ ገንዘብ ተከፍሎት ሌሎችም ግዢዎች እየፈፀመ የሚመረተው የኢንቨስትመንት ምርት ህዝብ የማይሸምተው ኢንቨስትመንት ሲስፋፋ ጥቅም ብቻ ሳይሆን ጉዳትም እንዳለው ይጠቅሳሉ።

አቶ ዓለማየሁ በበኩላቸው፤ ባለፉት አምስት ዓመታት የዋጋ ግሽበት እየጨመረ የቀጠለው በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም ጭምር መሆኑን ያስረዳሉ። የዓለም ኢኮኖሚ የተሳሰረ መሆኑን በማስታወስ፤ በምስራቅ አውሮፓ የተፈጠረው ጦርነት እና በአየር ጠባይ ለውጥ ምክንያት የተከሰተው የምርት ማነስ እንዲሁም ድርቅ እና ጎርፍ ምክንያቶች ናቸው ይላሉ።

ሌላው በአቶ ዓለማየሁ የተገለፀው፤ የዓለም ህዝብ ቁጥር ስምንት ቢሊየን ደርሷል። መሬት ግን መጠኗ አልጨመረም። ሕዝብ ሲጨምር ፍላጎት ይጨምራል። ሕዝብ ሲጨምር ተመጣጣኝ ምርት መጨመር አለበት። ምርት ካልጨመረ እጥረት ስለሚፈጠር የዋጋ ግሽበት ይከሰታል። በኢኮኖሚክስ ህግ መሰረት አቅርቦት እና ፍላጎት ዋጋን ይወስናል። አቅርቦት እና ፍላጎት ተመጣጣኝ ሲሆኑ ዋጋውን ገበያው ይወስነዋል። ፍላጎት ከአቅርቦት በላይ ከሆነ ዋጋ መጨመሩ ግልፅ ነው ይላሉ።

ወደ ኢትዮጵያም ሲመጣ ተመሳሳይ ነው የሚሉት አቶ ዓለማየሁ፤ የኢትዮጵያ ህዝብ ጨምሯል። ፍላጎቱም ከፍተኛ ነው። ድርቅ እና የፀጥታ ችግር አለ። ገበሬው በፀጥታ ችግር ምክንያት ማምረት ባለመቻሉ የምርት ማሽቆልቆል ነበር። በዚህ ዓመት የተሻለ የስንዴ ምርት ስለመመረቱ እየተገለፀ ነው። ምናልባት በያዝነው ዓመት የተመረተው እህል ወደ ገበያ ከገባ ዋጋ ሊረጋጋ ይችላል። ሌላው በኮቪድ ምክንያት የፋብሪካ ሰራተኛም ሆነ አገልግሎት ሰጪዎች ሥራ አቁመው ነበር። ይህ ደግሞ በዓለም ምርት መቀነስ ላይ የራሱን ተፅዕኖ አሳድሯል። ይሔ ተያይዞ የዋጋ ግሽበት ላይ የራሱ ሚና እንዳለው ይገልፃሉ።

የዶላር ዋጋ በየጊዜው መጨመሩ ለዋጋ ግሽበት አንዱ ምክንያት መሆኑን አቶ አለማየሁ ያነሳሉ። ነጋዴው ወጪውን ለማካካስ የልብስ፣ የጫማ፣ የቤት እቃ እና ሌሎችም ምርቶች ላይ ዋጋ ስለሚጨምር የዋጋ መረጋጋት አይኖርም። በዋናነት ግን ገበያውን የሚበጠብጡ ደላሎች መኖራቸውን በማስታወስ፤ በሌላ በኩል የዋጋ ግሽበት ላይ ራሱን የቻለ ትልቅ ጥናት መካሔድ አለበት ይላሉ።

አቶ ወሰንሰገድ ከአቶ ዓለማየሁ የተለየ ሃሳብ አላቸው። አቶ ወሰንሰገድ እንደሚሉት፤ ዋናው ትኩረት መደረግ ያለበት ምግብ ፣ መጠጥ፣ መጠለያ፣ እና የሚለበስ ምርት ላይ ነው። ከዛ ውጪ በቢሊየን ብር አውጥቶ ሕዝቡ ከሚያስፈልገው መሰረታዊ ምርት ውጪ የሆነ ኢንቨስትመንት ላይ ማዋል፤ ብር በብዛት ወደ ገበያው መበተን በራሱ ለዋጋ ግሽበት መንስኤ መሆኑን ያብራራሉ።

አቶ ወሰንሰገድ እንደሚገልፁት፤ ማንፋክቸሪንግ ፤ አግሮ ኢንዱስትሪ ወይም ከሰው ሕይወት ጋር በቀጥታ የተገናኘ ምርት ላይ ኢንቨስት ማድረግ ሲኖር የተበተነው ገንዘብ ገበያ ላይ ቢገባም ችግር አይፈጠርም። ሰው ወደ ገበያ ሔዶ የግብርና ምርቱን፤ ወተቱንም፣ ስጋውንም፣ ስንዴውንም ማግኘት ሲችል ዋጋው የሚረጋጋበት ሁኔታ ይኖራል ማለት ነው። ስለዚህ በእርሳቸው እምነት የዋጋ ግሽበቱ አንዱ መነሻ ኢንቨስት የሚደረግባቸው ዘርፎች በተገቢው መልኩ አለመመረጣቸው እና ከሰው ሕይወት ጋር በቀጥታ የተያያዙ አለመሆናቸው ነው።

ከውጭ ምንዛሪ ጋር ተያይዞም ያለውን ክፍተት ደግሞ ሲያብራሩ፤ በአሁኑ ጊዜ ያለው መረጃ እንደሚያመለክተው ወደ 20 ቢሊየን ዶላር የሚገመት ዕቃ በውጪ ምንዛሪ ወደ አገር ይገባል። ወደ ውጭ የሚላከው ግን ከአራት ቢሊየን አይበልጥም። ስለዚህ አገሪቱ የገቢ ምርት ጥገኛ ናት። ከነዳጅ ጀምሮ ሌሎች ጥሬ ዕቃዎች፣ ልብስ እና አጠቃላይ ጌጣጌጡን ጨምሮ የሚገባው ብዙ ነው። ወደ አገር የምታስገባው ምርት ብዙ የሆነባት አገር፤ የውጪ ምንዛሪዋን ዝቅ እንዲል ማድረግ የለባትም። ዝቅ ካለ ከውጪ የሚገባው ዕቃ በጣም ይወደዳል። በ100 ብር ሲገዛ የነበረው ዕቃ 800 ብር ሊገባ ይችላል በማለት በዚህኛው ሃሳብ ከአቶ ዓለማየሁ ጋር እንደሚስማሙ ያብራራሉ።

አቶ ወሰንሰገድ በመንግስት በኩል የተወሰዱ እርምጃዎችን በተመለከተ እንደሚናገሩት፤ ከብዙሃን የኢትዮጵያውያን ሕይወት ጋር ቀጥታ ግንኙነት የሌላቸው ከውጪ የሚገቡ ዕቃዎች መቆማቸው ለጊዜውም ቢሆን መፍትሔ ይኖረዋል። በእዚህ ምክንያት የዶላር መትረፍ እንዳለ ሆኖ ከቀረጡ የሚታጣው ግን ከሚተርፈው አንፃር ብዙ የሚባል ባለመሆኑ ትልቅ ውጤት ያስገኛል የሚል እምነት እንደሌላቸው ይናገራሉ።

እንደ አቶ ወሰንሰገድ ሁሉ የውጪ ምንዛሪ ብክነት ለመቀነስ ለጊዜው የቅንጦት ዕቃዎችን ማገዱ መልካም ነው የሚል እምነት እንዳላቸው የሚገልፁት አቶ ዓለማየሁ፤ አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ ለሚሸምተው ነገር ቅድሚያ መስጠቱ ተገቢ ነው። ከተወሰዱ መፍትሔዎች መካከል በየቀኑ በመሰረታዊነት ህዝቡ የሚጠቀምበት ዘይት በፍራንኮ ቫሉታ እንዲገባ መደረጉ መልካም ትክክለኛ እርምጃ መሆኑን ያነሳሉ። ነገር ግን ዘይትንም እዚሁ ሀገር ውስጥ ማምረት ያስፈልጋል። የቅንጦት ዕቃዎችም ቢሆኑ እንደታገዱ ከዘለቁም ጉዳት አላቸው፤ ኮንትሮባንድ ይስፋፋል። ሰዎች በህጋዊ መንገድ የተከለከሉትን ዕቃዎች ማግኘት ከፈለጉ ህገወጥ መንገድን እንደሚጠቀሙ ይገልፃሉ።

አቶ ዓለማየሁ እንዳብራሩት፤ የአገር ውስጥ ምርት ተትቶ የውጪውን ብቻ መጠቀም በአገር ላይ ጉዳት ያስከትላል። ቢሆንም ግን የአገሪቷ የዋጋ ግሽበት ከ30 እስከ 40 በመቶ ነው። የተወሰዱ የፖሊሲ እርምጃዎች ባይኖሩ ግን የበለጠ ከባድ ነበር። ለምሳሌ ዙምባብዌ ገንዘቧ በከፍተኛ መጠን ዋጋ አጥቷል። ግሽበቱም ከቁጥጥር ውጭ ሆኗል። በሽታውን፣ የተፈጥሮ አደጋውን፣ ጦርነቱን ተቋቁሞ የኢትዮጵያ ዋጋ ግሽበት እዚህ ደረጃ ላይ መድረስ በራሱ መልካም ነው ይላሉ።

መፍትሔ ያሉትን አቶ ወሰንሰገድ ሲጠቁሙ ፤ ዋናው የአገር ውስጥ ምርትን ማበረታታት ነው። ይሄ ከውጭ የሚገባን በአገር ውስጥ ለመተካት ያስችላል፤ የሥራ ዕድል ይፈጥራል። አቅርቦትን ያሰፋል። ስንዴ በስፋት ማምረቱ ትልቅ መፍትሔ ነው። የተትረፈረፈ ምርት በሀገር ውስጥ እንዲመረት ማድረግ ይገባል።

መፅሃፍም ያንተን ፍላጎት ካሟላሁ በኋላ ለወዳጅህ ለመስጠት እንድትችል አብልጠህ ሥራ ይላል። ማዕድ አጋራ ከሚለው ቀድሞ የሚለው አብልጠህ ሥራ ነው። የተመረተው ከተሰጠ አለቀ ማለት ነው። ነገር ግን ከመንፈሳዊ በረከት እና ከመተባበር አንፃር ከታየ ግን መልካም ነው ይላሉ።

አቶ ዓለማየሁ እንደሚገልፁት፤ ዕቃዎች እና አገልግሎቶችን በተመለከተ አቅርቦት ብቻውን መፍትሔ አይሆንም። ምርት በአንድ ጎን ሲኖር ገበያው ላይ የሚበተነው ገንዘብም ከፍተኛ ከሆነ የዋጋ ግሽበት ይፈጠራል። ብሔራዊ ባንክ የሚያትመው ገንዘብ ላይ ቁጥጥር ካልተደረገ በራሱ ለዋጋ ግሽበት መንስኤ መሆኑ አይቀርም። ብዙ አገሮች ገንዘባቸውን ሲያትሙ ፖሊሲ አላቸው። ከአጠቃላይ የአገር ምርት 10 ከመቶ ያልበለጠ ብር ያትማሉ። ከዛ በላይ ከሆነ ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት እንዳይመጣ መጠንቀቅ ያስፈልጋል ይላሉ።

ኢንቨስትመንት ከሌለ አገር አታድግም የሚሉት አቶ ዓለማየሁ፤ ኢንቨስትመንት ሲኖር ምርት ይገኛል፤ አገልግሎት ይጨምራል ፤ የሚገዛ እና የሚሸጥ ነገር ይኖራል። ነገር ግን ከኢኮኖሚው አቅም በላይ ከሆነና ተቀጥረው የሚሰሩ ሰዎች ከበዙ በእጃቸው ብር ይዘው ወደ ገበያ ይገባሉ። ስለዚህ ኢንቨስትመንቱም ቢሆን ከአቅም በላይ እንዳይሆን ቁጥጥርና ክትትል ያስፈልጋል። ኢንቨስትመንትም በጥንቃቄ መሆን እንዳለበት ይመክራሉ።

ዋናው መፍትሔ ግን ምርት መጨመር ነው። ገበሬ ብዙ ይለፋል፤ ብዙ አያመርትም፤ ስለዚህ መፍትሔው ዘመናዊ የእርሻ መሳሪያ፣ ምርጥ ዘር፣ ትራክተር እንዲሁም ኮምባይነር እንዲጠቀም ማድረግ ያስፈልጋል። በዘመናዊ አመራረት ዘዴ በመጠቀም፤ የተወሰኑ ጥቂት ገበሬዎች አገርን እንዲመግቡ መደረግ አለበት። በሌሎች አገሮች ሳይንሳዊ ቴክኖሎጂን ተጠቅመው ምርታማነትን በማሳደግ በአጭር ካፒታል ብዙ በማምረት ለውጥ እንደሚመጣ ታይቷል። ስለዚህ መፍትሔው የሰለጠነ የሰው ሃይልና ዘመናዊ ካፒታል አቀናጅቶ አገር መለወጥ መሆኑን ይጠቁማሉ።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# በሕገወጥ መንገድ ከአገር የወጡ ሴቶችና ፈተናዎቻቸው



ሰላማዊት ውቤ

ወይዘሮ ዓለምበዛ ጌታቸው የተወለደችው ደብረ ብርሃን ከተማ ውስጥ ነው። እናቷ በሞት የተለየቻት ትንሽ ከፍ እንዳለች ቢሆንም በውል አታውቃትም። አባቷ ማን እንደነበርና ይሙት ይኑርም መረጃው የላትም። ‹ስለ አባቴ የምጠይቀውና የሚያውቅም ሰውም የለም› ትላለች። ምክንያቱም እናቷ ስትሞት አብራት ትኖር የነበረችው ታላቅ እህቷም እንደነገረቻት ሁለት ወንድሞችም ነበሯት። ሆኖም አንዱ በሽተኛ ነበርና ሞቷል። ሌላው ደግሞ ጦር ሜዳ እንደሄደ ባለመመለሱ ይሙት ይኑር አይታወቅም።

እናቷ እንደሞተች ከጥቂት ዓመት በኋላ እህቷም ሞተችባት፤ በዚህን ጊዜ ነበር ወደ አዲስ አበባ የመጣችው። ቢሆንም ያኔ ትንሽ በመሆኗ አመጣጧን አታስታውስም። ግን ደግሞ እህቴ ስትሞት ነው የመጣሁት ትላለች። እዚህ አዲስ አበባ ውስጥ ከደረሰች በኋላ አንድ ሰው እንደ ልጅ ያሳድጋት ነበር።

በዚህ ሰው እጅ ስለማደጓ ስታወራ ሳግ ይይዛታል። እንባዋም ተናንቋት ብቻ አያቆምም። ስቃዩ አሁን አሁን እየደረሰባት ያለ ይመስል እንባዋ እርግፍ እርግፍ ይላል። ሰውዬው ምክንያቱን ባታውቅም ይገርፋት የነበረው ሁልጊዜ ነው። ሲገርፋት አሁን አሁን ስታስበው ሰው ደርሶ እንዳያስጥለው በሩን ይዘጋል። በር በመዝጋት ብቻ ሳያቆምም አፏ ውስጥ ጨርቅ ይጠቀጥቅባታል። ህመሙ መፈጠሯን እንድትጠላ የሚያደርግ ነበር። ግርፋቱን ያቆም የነበረው ዛሬም ከጀርባዋ፤ ከእግሮቿ፤ እጆቿና ፊቷ ላይ ያልጠፋው ሰንበር በሰውነቷ ሲወጣ ነው።

በዚህ ምሬት ብን ብላ ከቤቱ ጠፋች። ሰው ቤት ስራ ተቀጥራም መሥራት ጀመረች። የሰው ቤት ሠራተኝነት ኑሮ እንደ ሰውዬው ቤት በግርፋት የምትሰቃይበት ባይሆንም ብዙ ጣጣ ስላለው አይመችም። ባልና ሚስት ቤት ስትገባ መልከ ቀና በመሆኗ ባሌን አየሽው ብላ ሚስት ትጣላታለች። ባል በበኩሉ ሚስት በአካባቢው ከሌለች ይጎነትላታል። ቢሆንም ከአንዱ ቤት አንዱ ቤት እያለች ሕይወቷን በሰራተኝነት ኑሮ መግፋቷን ቀጠለች። በዚህ መካከል የገባችበት ወንደላጤ ሳታስብ ደፍሯት አረገዘች። አጋጣሚ ሆኖ ልትወልድ ትንሽ ሲቀራት ያ ድሮ ያሰቃያት የነበረው ሰውዬ በመሞቱ እህቱ እሷ ጋር ልጇን እንድትገላገል አደረገች። መልካም ሰው ነበረችና በጥሩ ሁኔታም አረሰቻት። ግን በኑሮ ምስኪን ስለነበረች ልጇን ለማሳደግ የግድ እሷ እየሰራች ማገዝ ነበረባት።

ስለዚህ ነው ወደ ሳዑዲ ለመሄድ የወሰነችው። የሄደችው በህጋዊ ኤጀንሲ በአውሮፕላን በመሆኑ መንገድ ላይ የገጠማት መከራ የለም። የሄደችበት ቀን የረመዳን በዓል ነበርና አሰሪዋ ብዙ ቀጣሪዎች እንደሚያደርጉት ሁሉ ከመካ ተቀብላት ወደ ቤት ይዛት ሄደች። ገላዋን ታጥባና የተሰጣትን ልብስ ለብሳ ወደሥራ ተሰማራች፤ ሥራው ከጉዞው ጋር ተዳምሮ እስኪያዳክማት ምግብ የሰጣት አልነበረምና ረሃብ ሲፀናባት አሰሪዎቿ አዛን ሲል ከሚቀምሱት ዳቦ ሰርቃ ጉያዋ ውስጥ በመደበቅ መብላቷን አትዘነጋውም።

ወደ ኢትዮጵያ የተመለሰችው ቀጣሪዋ እዛም እዚህም በምታሰራት ሥራ ጫና ተማራ ነው። ስትመለስ ሁለት ዓመት ያገለገለችበትን ደመወዝ አልከፈሏትም። “የሳዑዲ ቀጣሪዎች የሰሩበትን ደመወዝ ሲጠይቋቸው ሰርቃኛለች፤ ልጄን ደብድባብኛለችና ሰድባኛለች ብለው በሀሰት በመወንጀል ያሳስራሉ። በዚህ ምክንያት እስር ቤት ከምበሰብስ ደመወዜን ትቼ ብመጣ ይሻለኛል በማለት ከምትሰራበት ቤት መውጣቷን ትናገራለች።

አሁን ላይ እንደሷ መንግስት ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ያደረጋቸውን አምስት ሴቶች በማህበር እንዲደራጁ አድርጎ ሽገር ዳቦ ላይ እየሰሩ ይገኛሉ። የሚሰሩት በፈረቃ ሲሆን አንድ ሳምንት አንዳቸው አንድ ሳምንት ሌላቸው መሆኑንም ዓለምበዛ አጫውታናለች። ወጣት ሰናይት ደበበ አባት የሌለውን ልጇን ከወለደች በኋላ ብዙ የሕይወት ውጣ ውረድ አሳልፋለች። ሰርታ ለማግኘት ልጇን የሚይዝላት ከማጣት ጀምሮ የሚላስ የሚቀመስ እስከማጣት ደርሳለች። ይሄ የመጀመሪያው ሲሆን ሁለተኛውን ምዕራፍ መከራዋ የጀመረው ደግሞ ገና አረብ አገር ሳትሄድ ነው። ገንዘቡ ስላልነበራት ሌት እና ቀን በየሰው ቤት ልብስ በማጠብና የተለያዩ የቤት ሥራዎችን በመሥራት ጥሪት መቋጠር ነበረባት።

ሆኖም አዲስ አበባ ውስጥ ጥሪት ለመቋጠር ያደረገችው ጥረት አልተሳካላትም። እናም እንደ ልማዷ ከአዲስ አበባ ጠፍታ ወደ ናዝሬት ሄደች። እዚያም በየሰው ቤት እየዞረች ልብስ በማጠብ ልትቋጥረው ያሰበችው ጥሪት ሊሞላላት አልቻለም። የቤት ኪራዩን እንኳን ለምትሸፍንበት አልተርፍ አላት። በመሆኑም ከሰው ቤት ሥራው በተጓዳኝ ማታ ማታ እየቆመች በሴት አዳሪነት ሥራ ልትደጉመው ሞከረች። የሴተኛ አዳሪነት ሥራው እጅግ የሚያማርርና መፈጠርን የሚያስጠላ አስቀያሚ ነበር። መልከ መልካም በመሆኗ ብዙ ወንዶች ቢፈልጓትም ከተጠቀሙባት በኋላ ሳይከፍሏት የሚሄዱ ይበዛሉ። ዳጎስ ያለ ብር የሚከፍሏት ደግሞ ያለ ኮንዶም ግንኙነት ማድረግ ይፈልጋሉ። ይሄ ደግሞ ለእሷ በፍፁም የሚታሰብ አልነበረም። ምክንያቱም ጤናማ ሕይወቷን ሰርታ ለማደርና ነፍሷን ለማቆየት ብቻ ሳይሆን አንድዬ ልጇንም ለማሳደግ ትፈልገዋለች።

እናም ናዝሬት አልሆን ሲላት በአንድ ሹፌር ወዳጇ መካሪነት ወደ ድሬዳዋ ተሻገረች። የቦቴ ሹፌሩ ወዳጇ እዛ እንዳደረሳት የለመደችውን የሰው ቤት ሥራ ቀጠለች። እዚህ ምንም የምትከፍለው የቤት ኪራይ ባይኖርም የጫትና የሲጋራ ሱሰኛ ለመሆን በመዳረጓ ያሰበችውን ጥሪት መቋጠር አልሆነላትም። ከድሬድዋ ጅቡቲ ዘለቀች። እዚያ ያገኘቻትን አንዲት ሴት ከዚህ ቀደም እሷን ሳዑዲ አረብያ የላካት ሰው እንዳለና እሷንም እንደሚልካት ነገረቻት። ይሄ ሁሉ ሲሆን ልጇን ለያዘችላት ሴት ቤሳቤስቲን ሰጥታት አታውቅም ነበር ። ሰውዬው የተወሰነ ገንዘብ ከሰጠችው ሌላውን እዛ ከደረሰች በኋላ ሰርታ መክፈል እንደምትችል ሲነግራት ተደሰተች። ወደ ሳኡዲ አረቢያ በእግር ጉዞ ተጀመረ።

መነሻቸውን ጅቡቲ አድርገው መንገድ መጀመራቸውን እንጂ በየት ፤በየት አድርገው እንደሚሄዱ አልነገራትም። ግን በቶጎ ጫሌ በኩል አድርጎ ተመልሶ ወደ አርቲሼክ ነበር ያቀናው። የኮንትሮባንድ ከተማዋ አርቲሼክ ሲደርሱ ለደላላው ከአዲስ አበባ ስልክ ተደወለለት። በአይሮፕላን የሚወስዱ ኤጀንቶች ስላሉ በአዲስ አበባ በኩል ይሻላል አላት። ከሁለት ዓመት በላይ ጨቅላ ልጇን ለጣለችባት ምስኪን ሴት አንድ ነገር ሳትል መመለስ ስላሳፈራት 20ሺህ ብሯን እንዲመልስላት ጠየቀችው። እዚህ ድረስ የመጣሽበት ነው ብሎ ጥሏት ወደ አዲስ አበባ ተመለሰ።

ጥቂት ጊዜ አርቴሽክ ስትሰራ ቆይታ ጀልባ ተፈናጣ በመኪና ሳውዲ በመጨረሻ ሳኡዲ ለመድረስ በቃች። ‹‹ሲያወሩት እንዲህ ቀላል ቢመስልም ጉዞው እጅግ አስፈሪ፤ ከባድና አስጨናቂ ነበር›› ትላለ ። ጉዞውን በህንድ ውቂያኖስ ባህር ውስጥ ያደረገው ጀልባ እንደ ሰርዲን ለታጨቁት ተሳፋሪዎቹ ዋስትና የሚሰጥ አልነበረም። ባህሩን እየቀዘፈ ወደ የመን ሲከንፍ ወደ ባህሩ ለሚወድቁት ሰዎች ከአፍ የወደቀ ጥሬን ያህል እንኳን ትኩረት አይሰጥም።

እሷ ቀደም ብላ በጀልባው ውስጥ ቦታ በመያዟና መካከል በመሆኗ ባህር ውስጥ ከመውደቅ ብትተርፍም በጉዞው ያሳለፈችው ስቃይ ቀላል አልነበረም። “በሰው መጨናነቅና ሙቀት ታፍኜ መፈጠሬን የጠላሁበት ስቃይ ገጥሞኛል። ምን አልባት ብችል ባህር ውስጥ አንደ ወደቁት መውደቅም አስመኝቶኛል” ትላለች። ከየመን ወደ ሳውዲ የገባችበት የጭነት መኪና እንዲሁ እንደ እሷ ሰርተው በብርቱ መለወጥ በሚሹ እህቶቿ በመጨናነቁ በሕይወት የመኖር እስትንፋስን የሚቆርጥ ነበር። መኪናውን ለመያዝ ረጅም በረሃ በእግሯ መጓዝም ነበረባት። ረሀቡ፤ውሃ ጥሙና ድካሙ መቼም የሚረሳት አልነበረም። እጅግ ተጎሳቁላና ከሰውነት ተራ ወጥታም ነበር። እንዲህ ሆና ሳዑዲ ደረሰች።

ከመኪናው ወርዳ ወደ ቀጣሪዋ የሚወስዳትን ሰው ሌሎች በርካታ ሴቶች የሚጠባበቁበት ሥፍራ ሆና ስትጠብቅ ፖሊስ ደርሶና አፋፍሶ እሷንና አብረዋት የነበሩትን በሙሉ ወደ እስር ቤት አስገባቸው። “ አብረውኝ እስር ቤት ከነበሩት ብዙዎቹ ወዲያው ወጥተዋል። ዓመትና ሁለት ዓመት ቆይተው የወጡም አሉ። ምክንያቱም እነሱ ያመጧቸው ደላሎች ጉዳያቸውን ይከታተሉላቸው ነበር። እኔን ያመጣኝ ደላላ ግን ከነጭራሹ ረስቶኛል” የምትለው ሰናይት በሳዑዲ እስር ቤት ከ10 ዓመት በላይ በእስር ቆይታ በኢትዮጵያ መንግስት አማካኝነት በቅርቡ ወደ አገሯ መመለሷን ትናገራለች። ሰናይት እንኳን ከባርነት ነፃ ወጥቼ ተመለስኩ። በሀገሬ ላይ ሰርቼ እለወጣለሁ የሚል ተስፋም ሰንቃለች። በተለይም መንግስት አዲስ በጀመረው የሌማት ትሩፋት ዘርፍ በመሰማራት በዶሮ እርባታ፤ በወተት ምርትና በተለያዩ አትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ በመሳተፍ እራሷን ለመቀየር ዕቅድ አላት።

የገበሬ ልጅ የሆነችው ሰሚራ መሐመድ ሌላዋ በመንግስት አማካኝነት በቅርቡ ወደ አገሯ የተመለሰችና በአዲስ አበባ በሚገኝ በአንድ የተመላሾች መጠለያ ጣቢያ የምትገኝ ወጣት ናት። ዕድሜዋ 28 ሲሆን በሳዑዲ ያሳለፈችው የእንግልትና የመከራ ሕይወት የ40 ዓመት ሴት አስመስሏታል። ስለ ራሷና አካሄዷ እንደነገረችን አባቷና ቤተሰቦቿ ባለፈው ሦስት ዓመት በነበረው የእርስ በእርስ ግጭት መሞታቸውንና ቤት ንብረታቸው መውደሙን ሰምታለች።

በየማሳው እየዞረ የሆነ ያልሆነውን ቀባጥሮ የአርሶ አደር ልጆች በማታለል በሚያስኮበልል ደላላ አማካኝነት ነው ወደ ሳዑዲ አረብያ የሄደችው። በእርግጥ ደህና ብር ከአባቷ ተቀብላ ለደላላው በመስጠቷ የላካት በአውሮፕላን በመሆኑ እንደሌሎች እህቶቿ በመንገድ ላይ የደረሰባት እንግልትና መከራ አልነበረም።

ሳዑዲ እንደደረሰች ቀጣሪዋ ከመካ ተቀበለቻት። ፈጥናም ፓስፖርቷን ወሰደችባት። በወቅቱ ቆይታ ትመልሳልኛለች ብላ አስባ ስለነበር ምንም አልተናገረችም። እቤት እንደደረሱ ተፈተሸች። የያዘችውን ልብስ ጋርቤጅ አስጥላ አዳዲስ ልብሶች በመስጠት ገላዋን እንድትታጠብ አደረገቻት። ኢትዮጵያዊያዋ ሠራተኛዋ የእንቅልፍ ሰዓቷ ስለነበር ምንም ሳታርፍ ከመንገድ እንደመጣች ቀጥታ ወደ ሥራ እንድትገባ አደረገቻት። ቤት በማጽዳት ብቻ ሌሊቱ ነጋ።

በጽዳቱ ማዳም አልረካችም። ያፀዳችውን ቤት ድጋሚ እንድታፀዳ በቁጣ አዘዘቻት። ትዕዛዟ የንቀት ዕይታ የታከለበት ነበር። በእርግጥ ወደ ሳዑዲ ስትመጣ የቤት ጽዳትም ሆነ ሌላ የሙያ ስልጠና አልወሰደችም። ሌላው ቀርቶ የቀለም ትምህርትም አልነበራት። የቀጣሪዋ የንቀት አተያይ ቢያናድዳትም ልምድ የሌላት መሆኑን ታሳቢ አድርጋ ድጋሚ ቤቱን አፀዳች። ሰሚራ ሥራዋ ጽዳት ብቻ ነበር። የቤት ብቻ ሳይሆን ልብስን ጨምሮ ማንኛውም ጽዳት ሥራ እሷን የሚመለከት መሆኑን አወቀች። ሆኖም ይሄን ሥራ የምትሰራው ቀጣሪዋ ቤት ውስጥ ብቻ አልነበረም። እናቷ ቤት በመኪና ወስዳ ዕለት ከዕለት ታሰራት ነበር።

አንዲት ኢትዮጵያዊት ባልደረባዋ እስክትነግራትና ሁለት ዓመት እስኪሞላት የአሰራር ስርዓት እንጂ ማዳሟ የጫነችባት የበደል ቀንበር አይመስላትም ነበር። ከዕውነታው ጋር ተዳምሮ ጫናው እየሰለቻት፤ እየከበዳትና እያዳከማት ስትመጣ እናቷ ቤት ሄዳ ተጨማሪ ሥራ ለመሥራት ፈቃደኛ እንዳልሆነች ለአሰሪዋ ነገረቻት። በዚህም ከአሰሪዋ ጋር ተጋጩ። ከመካ ወደ ቤት ስታመጣ ተቀብላት ያስቀመጠችውን ፓስፖርቷን እንድትመልስላት ብትጠይቃት በካፋላ ሕግ ስርአት የሚቀመጠው እሷ ጋር በመሆኑ ልትመልስላት እንደማትችል ነገረቻት። ከቀጣሪዋ ቤት ለመጥፋት ዕቃዋን ስትሰበስብ ይሄን የባርነት የአሰሪና ሠራተኛ አገዛዝ እንድትቃወምና መብቷን እንድታስከብር ግንዛቤ ያስጨበጠቻት ኢትዮጵያዊቷ ባልደራዋ ሕገወጥ ተብላ በፖሊስ ለመያዝ ማቀዷን ገለፀችላት። ሰሚራ ሁለት ዓመት ሊሞላትና ኮንትራቷን ልትጨርስ የጥቂት ወራት ዕድሜ ስለቀራት እዛም እዚህም እንደ ባሪያ ሴት ከቀን እያገለገለች ቀጣሪዋ ጋር ለመቀመጥ ተገደደች።

ማዳሟ ቀደም ብላ ቀጥራት የነበረችውን ኢትዮጵያዊቷን ባልደረባዋን መክረሽ ልታበሪብኝ የነበርሽው አንቺ ነሽ በማለት ኮንትራቷ ሳያልቅ ወደ ኢትዮጵያ መለሰቻት። አሁን ይባስ ብሎ ወደ አገሯ የተመለሰችው ባልደረባዋ ትሰራው የነበረውን ጨምሮ አጠቃላዩ የቤት ሥራ የሰሚራ ሆነ። እስከ ሁለት ዓመት እንደምንም ተቋቁማው ቆየችና ወደ አገሯ እንድትመልሳት ጠየቀቻት። “ሆኖም ዛሬ ነገ እልክሻለሁ እያለች ቪዛና ውሏን ሳታድስላት ቀረች፤ ሰሚራ በዚህ ምክንያት ሳዑዲ ውስጥ መንቀሳቀስ ባለመቻሏ ጉልበቷ ለበርካታ ዓመታት በአሰሪዋ ሲበዘበዝ መቆየቱን በምሬት ትናገራለች።

ለመጥፋት በሞከረችበት ወቅት የተሳፈረችበት ታክሲ ሾፌር ደስ አልሽኝ በማለት አባላዋን ገፎ ሊስማት ሲሞክር በመቃወሟ፤ ”ለዚህ ነው እንዴ የሚገርምሽ” በማለት አሳቻ ቦታ ወስዶ ሊደፍራት በማሰብ አቅጣጫውን ለውጦ ሲነዳ ዘላ በመውረድ አደጋ ደርሶባታል። ለዓመታት በነፃ ስታገለግል ቆይታ በምሬት ጥላ በወጣችበት ወቅት ደግሞ ህገወጥ ተብላ ዘብጥያ ለመውረድ በቅታለች ፤ ከዓመታት በኋላ በመንግስት አማካኝነት ወደ አገሯ ለመመለስ መቻሏንም ታወሳለች።

‹በህገወጥ መንገድ ከሀገር ወጥተው በእንዲህ ዓይነት አስቸጋሪ ሁኔታ ከሚገኙት መካከል ካለፈው ሚያዝያ 2014 ዓ.ም ጀምሮ 84 ሺህ 258 ዜጎችን መልሰናል። አሁንም እየመለስን እንገኛለን›› የሚሉት ደግሞ በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሕገወጥ ዝውውር መከላከልና የተመላሽ ዜጎች ድጋፍና ክትትል አስፈፃሚ ዳይሬክቶሬት ኃላፊ አቶ ደረጀ ፈቅይበሉ ናቸው። መንግስት ዜጎቹ በሀገራቸው ተከብረው እንዲሰሩ ለማስቻል ሁኔታዎችን አመቻችቶ በማህበር ተደራጅተውና በግል ወደ ሥራ እንዲገቡ እያደረገ ነው።

በተለይም በግብርና ዘርፍ እና የዚሁ አካል በሆነው በሌማት ትሩፋት ከአረብ ሀገር ተመላሽ ሴቶችን የስራ ዕድል ተጠቃሚ ለማድረግ መታቀዱንም ገልጸውልናል።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

ትላንትናን መሰረት አድርጎ ዛሬን የገነባው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ትላንት እንዴትና ምን ይመስል ነበር፣ ምን አይነት ሀገራዊ ኩነቶችና ክስተቶችንስ በማህደሩ ላይ ከትቦ አልፏል? የሚሉትን ሀሳቦች የኋልዮሽ የሚቃኝበት 'አዲስ ዘመን ድሮ' እንደተለመደው ዛሬም ልዩ ልዩ ዜናዎችን ቀነጫጭቦ አቅርቦላችኋል። በዛሬው አምዳችን በዋናነት የደርግ መንግስት አብዮት በተጧጧፈበት 1960ዎቹ መጨረሻ የተዘገቡ ጉዳዮችን መራርጠናል። በተደጋጋሚ ይጋጩ የነበሩት ሁለቱ ጎሳዎች እርቅ ስለመፈጸማቸው፣ በዱላ ብቻ የጦር መሳሪያ ስለማረከው ጀግና፣ የቀድሞው የቤጌምድርና ሰሜን ስም መቀየሩ፣ ስለተዘጉት ሶስቱ ፍርድ ቤቶች፣ የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ ወዛደሮች መታጠቃቸው እንዲሁም ኢትዮጵያን ስለጎበኙት ታላቁ የነጻነት ታጋይ ፊደል ካስትሮን የተመለከቱ ዜናዎች ተካተዋል።

### ይጋጩ የነበሩት ጎሣዎች ታርቀው ሠርጎ ገቦችን ለመደምሰስ ወሰኑ

ሐረር(ኢ.ዜ.አ) ሐረርጌ ክፍለ ሀገር በደገሃቡር ወረዳ በሂግሊሴ ቀበሌ የሚኖሩት ሬር መገንፊቅ የሬር ሸርማርኬ ጎሳዎች ከሰባት አመት በላይ በመካከላቸው የነበረውን የነፍስ ግድያና የዝርፊያ ቅራኔ ሰሞኑን በእርቅ አስወገዱ።

ሁለቱም ጎሣዎች በመካከላቸው የነበረውን ቅራኔ ከማስወገዳቸውም በላይ ለመደብ ትግል ክንዳቸውን በማስተባበር ፊውዳሊዝምን፣ ኢምፔሪያሊዝምንና ቢሮክራሲ ካፒታሊዝምን ለመደምሰስ ተስማምተዋል።

ከዚህም ሌላ በጎረቤት አገር በኩል ሠርገው የሚገቡትን ወንበዴዎች ለመደምሰስ ወስነዋል።

ማክሰኞ መጋቢት 26/1969ዓ.ም

### ገበሬው በዱላ የጦር መሣሪያ ማረከ

በወገራ ወረዳ በልማምያ ቀበሌ ገበሬ ማህበራት ሊቀ መንበር የሆነው ደበበ በላይ ሰሞኑን መሣሪያ ያነገቡ አራት የኢዲዩ ወንበዴዎች ከመኖሪያ ቤቱ ድረስ በመሄድ ሊገድሉት ሲሞክሩ በያዘው ዱላ ብቻ ተከላክሎ ምንም አይነት ጉዳት ሳይደርስበት አንድ የጦር መሣሪያቸውን የማረከባቸው መሆኑን ተገለጠ።

ሊቀመንበሩ አደጋ ሊያደርሱበት ከቃጡት ከእነዚሁ ወንበዴዎች ተከላክሎ የማረከው የጦር መሣሪያ አንድ ዲሞፍተር ጠመንጃ መሆኑን የወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት አስታውቋል።

ሐሙስ ሚያዝያ 27/1969ዓ.ም

### የቤጌምድርና ሰሜን ስም ተለወጠ

የቤጌምድርና ሰሜን ክፍለ ሀገር ይባል የነበረው ከትላንት ጀምሮ የጎንደር ክፍለ ሀገር ተብሎ እንዲጠራ የተወሰነ መሆኑን የአገር አስተዳደር ሚኒስቴር ትናንት አስታወቀ።

እሑድ ታህሳስ 13/1969ዓ.ም

### ባለጉዳይ በመጥፋቱ በሦስት ወረዳዎች መደበኛ ፍርድ ቤቶች ተዘጉ

አርባ ምንጭ፣(ኢ.ዜ.አ) በጋሞ ጎፋ ክፍለ ሀገር ከንባ፣ ምዕራብ አባያ፣ ዲታ በተባሉት ወረዳዎች የነበሩት መደበኛ ፍ/ቤቶች የሚያስተናግዱት ባለጉዳይ ባለማግኘታቸው መዘጋጀታቸውን የክፍለ ሀገሩ የከፍተኛ ፍ/ቤት ሰብሳቢና ተጠሪ ዳኛ ገለጡ።

አርብ ነሐሴ 14/1969ዓ.ም

### የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ ወዝአደሮች ታጠቁ

ሰፊው ሕዝብ የመጣለትን አብዮት ከውስጥና ከውጭ ቀልባሽ ኃይሎች መከላከል ይችል ዘንድ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ አብዮቱ ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ከተሸጋገረ ወዲህ ጭቁኑን እርሶ አደርና ወዝአደር ለማስታጠቅ በገባው ቃል መሠረት ባለፈው እሑድ ከቀትር በላይ የመተሐራን ወዝአደሮች አስታጥቋል።

በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወዝአደሮች ተካፋይ በሆኑበት ሰልፍ ላይ ትጥቁን ዘጠኝ አባላት ላሉት የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ ወዝአደሮች የአብዮት ጥበቃ ኮሚቴ ያስረከቡት 50 አለቃ ለገሰ አስፋው የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የወታደራዊ ክፍሎች የፖለቲካ ጉዳይ ኃላፊና የጊዜያዊ የትጥቅ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሊቀመንበር ናቸው።

**ማክሰኞ ሐምሌ 16/1969ዓ.ም**

### ኢትዮጵያን መድፈር በእሳት መጫወት መሆኑን ሶቪየት ሕብረት ገለጠች

በኅብረተሰብአዊት ለኢትዮጵያ ላይ በሱዳን መንግሥት ባለሥልጣኖች በኢምፔሪያሊስቶችና በአድኃሪ ሀይሎች ድጋፍ ወረራ በመዘጋጀት ላይ መሆኑን ታስ የተባለው የሶቪየት ዜና አገልግሎት ባለፈው እሑድ ከሞስኮ አስታወቀ።

*****

በኢትዮጵያ ላይ ወረራ ለመፈጸም የሚደረገውን ዝግጅት በሚመለከተው ጉዳይ ታስ ባለፈው እሑድ ያወጣው መግለጫ ሙሉ ቃል የሚከተለው ነው።

"በኢትዮጵያ ላይ ወረራ ለመፈጸም ዝግጅት በመደረግ ላይ መሆኑን የሚያመለክቱ ዜናዎች ከጥቂት ጊዜ ወዲህ ከልዩ ልዩ ክፍሎች ይሰማሉ። በዜናዎች መሰረት መደበኛ ወታደሮች ወደ ምዕራብ ኢትዮጵያ ወሰን በመላክ ላይ ናቸው። የታጠቁ ቡድኖች ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ሰርገው እየገቡ ለፀረ-አብዮተኞችና ለተገንጣይ ቡድኖች የሚሰጡት ድጋፍ እንዲያፋፍሙ እየተደረገ ነው። ሁኔታው ከኢትዮጵያ ጋር ወታደራዊ ግጭት እንዲነሳ ለማድረግና በሀገሪቱ ውስጥ ያለውን ተራማጅ መንግሥት ለመገልበጥ የሚቃጣ ነው። ይህ ሁሉ እንቅስቃሴ የሚደረገው በሱዳን ባለስልጣኖችና እንዲሁም በኢምፔሪያሊስት አድኃሪ ኃይሎች ሙሉ ተካፋይነት መሆኑ ግልጽ ነው።

******

በኢትዮጵያና በሶቪየት ኅብረት መካከል የሚደረገውን የወዳጅነት ግንኙነትና ተራድኦ በሚመለከተው የሁለቱ አገሮች የጋራ መግለጫ መሰረት ከኢትዮጵያ ጋር ግንኙነቷን በማጠናከር ላይ የምትገኘው ሶቪየት ኅብረት በኢትዮጵያ አካባቢ የሚደረገውን ሁኔታ በቅርብ ትከታተለዋለች። ታስም ሶቪየት ኅብረት፣ በኢትዮጵያ ላይ ወረራ ተግባር ለመፈጸም በመዘጋጀት ላይ የሚገኙትና በዚሁ እቅድ እንዲቀጥሉ የሚገፏፏቸውን ክፍሎች የምታወግዝ መሆኗን እንዲገልጽ ሥልጣን ተሰጥቶታል። አድራጎቱ በእሳት እንደሚጫወት እንደሚቆጠርና ራሳቸውን በዚሁ ጉዳይ ለሚያስገቡ በአፍሪካ ሕዝቦችና በመላው ዓለም ላይ ለሚፈጠሩ ችግሮች በኃላፊነት ይጠየቃሉ።

እሮብ ሚያዝያ 26/1969 ዓ.ም

### ጓድ ካስትሮ ኢትዮጵያን ለመጎብኘት መጡ

የኩባ ኮሚኒስት ፓርቲ ዋና ጸሐፊና የሚንስትሮች ምክር ቤት ሊቀመንበር ዶክተር ፊደል ካስትሮ ሩዝ ኢትዮጵያን ለመጎብኘት ትላንት ከእኩለ ቀን በኋላ አዲስ አበባ ገብተዋል።

ከዶክተር ፊደል ካስትሮም ጋር ለጉብኝት ወደ ኢትዮጵያ ከመጡት መልዕክተኞች መካከል የኩባ ኮሚኒስት ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴ፣ የፖለቲካ ቢሮ አባልና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ምክትል ሊቀመንበር ጓድ ክርሎስ ረፍዬል ሮድርጉስ ይገኙበታል።

ማክሰኞ መጋቢት 6/1969 ዓ.ም

# ዓለም አቀፍ




## ቻይና ከሦስት ዓመታት በኋላ ድንበሯን ለጎብኚዎች ክፍት አደረገች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ቻይና ከሦስት ዓመታት በፊት የኮቪድ-19 ወረርሽን ተከትሎ የዘጋችውን ድንብሯ ለጎበኚዎች ክፍት ማድረጓ ቢቢሲ ዘገበ፡፡

እንደ ዘገባው፣ አሁን ላይ የገቢ መንገደኞች ማቆያ ስፍራ መቆየት ሳያስፈልጋቸው በቀጥታ መግባት ይችላሉ። ይሁንና ገቢ መንገደኞች በ48 ሰዓታት ውስጥ የወሰዱትን የክትባት ማስረጃ ማቅረብ ይጠቅባቸዋል። እርምጃው በርካታ ቤተሰቦች በእገዳው ምክንያት ሳይገናኙ በመቆየታቸው ቻይና ድንበሯን መክፈቷ እንዳስደሰታቸው በመላው ዓለም የሚገኙ ቻይናዊያን ዘንድ ደስታን ፈጥሯል።

ከሆንግ ኮንግ ብቻ በቀጣይ ሳምንታት ግማሽ ሚሊዮን የሚጠጉ ቻይናዊያን ወደ ቻይና እንደሚገቡ የሚጠበቅ ሲሆን ከወዲሁ በአየር መንገዶች አካባቢ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ሰልፎች እየታዩ ነው። ምክንያቱም ብዙ ቤተሰቦች በገደቡ ምክንያት ሳይገናኙ ቆይተዋል።

"ቃላት የለኝም፤ እጅግ ተደስቻለሁ" ያለች አንድ ሌላ ተጓዥ ለሮይተርስ እንደተናገረችው ካንሰር እየተሰቃዩ ያሉ ወላጇን ለሦስት ዓመት ማየት እንዳልቻለች ተናግራለች። ይህ የጉዞ ገደብ የተነሳበት ወቅት ደግሞ ከቻይናዎቹ አዲስ ዓመት ጋር መገጣጠሙ ትልቅ ፈንጠዚያን ፈጥሯል።

የቻይናዎች አዲስ ዓመት በዓለም ላይ ከፍተኛ የሰዎች እንቅስቃሴ የሚደረግበት ሲሆን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ቻይናዊያን ቤተሰባቸውን ለመጠየቅና በዓሉን ለማክበር ከግዛት ግዛት ይንቀሳቀሳሉ። ከአውሮፓና አሜሪካም እንዲሁ በርካቶች ወደ ቻይና የሚያቀኑበት ወቅት ነው።

የቻይና መንግሥት ባወጣው አሃዝ በዚህ አዲስ ዓመት ብቻ 2 ቢሊዮን ጉዞዎች ይደረጋሉ። ይህ ከባለፈው ዘመን ጋር ሲነጻጸር እጥፍ ይሆናል።

የኅብረተሰብ ጤና ባለሙያዎች ይህ ከፍተኛ የሰዎች እንቅስቃሴ በድንገት ክፍት መደረጉ ወረርሽኙን ከቁጥጥር ውጭ ሊያስወጣው ይችላል ይላሉ። በቻይና አሁንም ቢሆን ከፍተኛ የሆነ የተህዋሲው ስርጭት እንዳለ ይነገራል።

## የቀድሞ የብራዚል ፕሬዝዳንት ደጋፊዎች የሀገሪቱ ቤተ መንግሥት ተቆጣጠሩ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- በቅርቡ በምርጫ ከስልጣን የተነሱት አክራሪው የቀድሞ የብራዚል ፕሬዝዳንት ዣየር ቦልሶናሮ ደጋፊዎች በነውጥ የሀገሪቱ ቤተመንግስት መቆጣጠራቸው ተገለጸ።

በግራ ዘመም የፖለቲካ መሪ ሉዊዝ ኢናሲዮ ሉላ ዳ ሲልቫ የተሸነፉት ቦልሶናሮ፣ የብራዚል የኤሌክትሮኒክስ የምርጫ ስርዓት ለማጭበርበር የተጋለጠ ነው የሚለውን ክስ ማቅረባቸውን ተከትሎ ደጋፊዎቻቸውን ለነውጥ እንዲነሳሱ መቀስቀሳቸው ይነገራል።

በዚህም በሺህ የሚቆጠሩ ቢጫ አረንጓዴ በለበሱ ተቃዋሚዎች በመዲናዋ ከፍተኛ ውድመት ማድረሳቸውንም ሮይተርስ ዘግቧል። ነውጡ የተነሳው ሉላ ወደ ሳኦ ፓውሎ ግዛት ይፋዊ ጉዞ ላይ ከዋና ከተማው ርቀው በቆዩበት ጊዜ መሆኑም ነው የተገለጸው።

የቴሌቭዥን ምስሎች ተቃዋሚዎች ጠቅላይ ፍርድ ቤቱን እና የሀገሪቱ ፓርላማን ሰብረው በመግባት መፈክሮችን ሲያሰሙ እና የቤት እቃዎችን ሲሰባብሩ ያሳያሉ።

በነውጡ ወደ 3 ሺህ ሰዎች መሳተፋቸውም የሀገር ውስጥ ሚዲያዎች መረጃ ያመለክታል።

የትናንቱ ነውጥ ምን አልባትም ከቀናት በፊት ቃለ መሃላ በፈጸሙት በአዲሱ የብራዚል ፕሬዝዳንት ሉዊዝ ኢናሲዮ ሉላ ዳ ሲልቫ ላይ ያነጣጠረ የመንፍቅለ መንግስት ሙከራ ሊሆን ይችላል ተብሏል።

ሉላ በበዓለ ሲመታቸው ባደረጉት ንግግር በቦልሶናሮ ብሔርተኝነት ሕዝባዊነት የተበጣጠሰች ሀገርን አንድ ለማድረግ ቃል መግባታቸው አይዘነጋም።

ይህ የሉላ ንግግርም ታዲያ አክራሪ ብሔርተኛውን የቀድሞ ፕሬዝዳንት ቦልሶናሮ ሊያበሳጭ እንደሚችል ይገለጻል።

በምርጫው ከተሸነፉ በኋላ በአደባባይ ብዙም ያልተናገሩት ቦልሶናሮ የስልጣን ዘመናቸው ሊጠናቀቅ 48 ሰዓታት ሲቀረው ብራዚልን ለቀው ወደ ፍሎሪዳ በማቅናታቸው በሉላ በዓለ ሲመት ላይ አልተገኙም።

ደጋፊዎቻቸው ይህን አመጽ በሚቀሰቀስበት ወቅት የቀድሞ ፕሬዝዳንት ዣየር ቦልሶናሮ አሜሪካ መገኘት ደግሞ ሌላው ነገሮች በጥርጣሬ እንዲታዩ ያደረግ ምክንያት እንደሆነ ይነገራል።

በተለይም በቅርቡ የቦልሶናሮ ወንድ ልጅ ኤድዋርዶ ከትራምፕ አማካሪዎች ጃሰን ሚለር እና ስቲቭ ባነን ጋር መገናኘቱን እና ምናልባትም የነውጥ ሴራው የተጠነሰሰው በጋራ ሊሆን ይችላል የሚሉ መረጃዎች እየወጡ ነው።

ያም ሆኖ በብራዚል የተነሳውን ነውጥ በተመለከተ የተጠየቁት የቦልሶናሮ ቤተሰብ ጠበቃ ፍሬድሪክ ዋሴፍ በጉዳዩ ላይ አስተያየት ከመስጠት ተቆጥበዋል።

ፕሬዝዳንት ሉላ ዳ ሲልቫ በቀጥታ የቴሌቪዥን ስርጭት በመግባት ይህ ተግባር ላይ የተሳተፉ በሙሉ በቁጥጥር ስር ውለው ጥብቅ ቅጣት እንደሚሰጣቸው ቃል ገብተዋል።

በዋና ከተማዋ ፕራዚሊያም ፖሊስ በሙሉ ኃይል ወጥቶ ሰላምና ጸጥታ እንዲያሰፍንም ጠይቀዋል ፕሬዝዳንቱ።

ነውጠኞቹን "የፋሺስት ርዝራዦች" ናቸው ሲሉ የጠሩት ፕሬዝዳንቱ ፤ ፋሺስቶች በብራዚል ታሪክ ሆኖ የማያውቅ ነውር ፈጽመዋል እናም የእጃቸውን ያገኛሉ ሲሉም ዝተዋል።

እስካሁን በተወሰደው እርምጃ በመቶዎች የሚቆጠሩ በነውጡ የተሳተፉ ዜጎች በቁጥጥር ስር የዋሉ ሲሆን የብራዚሊያን ከተማን ገዥ ኢባኒየስ ሮቻ ከስልጣን እንዲነሱ ተደርጓል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ጆ-ባይደንን ጨምሮ በርካታ የዓለም መሪዎች ድርጊቱን ኮንነዋል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ማክሰኞ ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ሰለሞን ባረጋ በኤልጎይባር አገር አቋራጭ ውድድር አሸነፈ

**ቦጋለ አበበ**

የቶኪዮ 2020 ኦሊምፒክ የ10ሺ ሜትር ቻምፒዮኑ አትሌት ሰለሞን ባረጋ በስፔን ኤልጎይባር በተካሄደ የ10 ኪሎ ሜትር አገር አቋራጭ ውድድር ድል ቀንቶታል። በታሪካዊው ስፔናዊ አትሌት ሁዋን ሙጉዌርዛ መታሰቢያነት የሚካሄደው ይህ ዓመታዊ አገር አቋራጭ ከትናንት በስቲያ ለሰባ ዘጠነኛ ጊዜ ሲካሄድ ወጣቱ አትሌት ሰለሞን ባረጋ በድንቅ የአጨራረስ ብቃት ለሁለተኛ ጊዜ የውድድሩ አሸናፊ መሆን ችሏል።

ከቶኪዮ ኦሊምፒክ ድሉ በኋላ በተለይም ባለፈው አንድ ዓመት ያህል በኦሪገኑ የዓለም ቻምፒዮናና በተለያዩ የጎዳና ላይ ውድድሮች ከድል ርቆ የቆየው ሰለሞን ከሳምንት በፊትም ሱሉልታ በተካሄደው የጃንሜዳ ኢንተርናሽናል አገር አቋራጭ ቻምፒዮና ውድድር ላይ በህመም ምክንያት ውጤታማ ሳይሆን ቀርቷል። በዚህም በቀጣይ አውስትራሊያ በሚካሄደው የዓለም አገር አቋራጭ ቻምፒዮና ላይ ኢትዮጵያን ከሚወክሉ አትሌቶች አንዱ ሳይሆን ቀርቷል። ይሁን እንጂ ሰለሞን በአስር ቀናት ልዩነት ትልቅ ትኩረት በሚሰጠው ኤልጎይባር አገር አቋራጭ ውድድር በ33 ደቂቃ ከ14 ሴኮንድ አሸናፊ መሆን ችሏል።

በወንዶች መካከል በተካሄደው የ10 ኪሎ ሜትር ውድድር ሰለሞን ባረጋ አስደናቂ የግል አጨራረስ ብቃቱን በመጠቀም በውድድሩ የመጨረሻ ሜትሮች ፍጥነቱን በመጨመር ከሌሎች ተፎካካሪዎቹ ተነጥሎ በመውጣት ነው ለድል የበቃው።

ሰለሞን የሁዋን ሙጉዌርዛ የአገር አቋራጭ ቻምፒዮናን ሲያሸንፉ የአሁኑ ለሁለተኛ ጊዜ ሲሆን እአአ በ2018 የውድድሩ አሸናፊ እንደነበር ይታወሳል።



አትሌት ሰለሞን ባረጋ ለሁለተኛ ጊዜ በኤልጎይባር አገር አቋራጭ ውድድር ማሸነፍ ችሏል፣

በትውልድ ኢትዮጵያዊ በዜግነት ባህሬናዊው የሆነው አትሌት ብርሃኑ ባለው ሰለሞንን ተከትሎ ሁለተኛ ደረጃን ይዞ ሲያጠናቅቅ፣ ትውልደ ሞሮኳዊው ስፔናዊ አትሌት አዴል ሜቻል ሶስተኛ ደረጃን ይዞ አጠናቋል።

በተመሳሳይ በሴቶች መካከል በተካሄደው የ8 ኪሎ ሜትር ውድድር ኤርትራዊቷ አትሌት ራሔል ዳንኤል አሸንፋለች። ኬንያዊቷ አትሌት ኤዲናህ ጄቢቶክ ሁለተኛ እንዲሁም በትውልድ ኬንያዊ በዜግነት ባህሬናዊ የሆነችው አትሌት ዊንፍሬድ ያቪ በቅደም ተከተል ሁለተኛ እና ሶስተኛን ደረጃ ይዘዋል አጠናቀዋል።

በስፔን የኢንዱስትሪ ከተማ ኤልጎይባር በየዓመቱ የሚካሄደው ይህ ውድድር እኤአ በ1937 ሕይወቱ ያለፈውን ታሪካዊውን ስፔናዊ የመካከለኛ ርቀት አትሌት ሁዋን ሙጉዌርዛ መታሰቢያ ሲሆን የዓለማችን ኮከብ አትሌቶችም ጠንካራ ፉክክር የሚያደርጉበት ነው። ኢትዮጵያውያን አትሌቶችም ከዚህ ውድድር ጋር ለረጅም ዓመታት የስኬታማነት ታሪክና ልዩ ቁርኝት አላቸው።

በስፔን ውስጥ በምትገኛዋ የባስክ ግዛት ኤልጎይባር ለረጅም ዓመታት ሲካሄድ የቆየው ይህ ውድድር እኤአ ከ1943 ጀምሮ ስያሜውን በእውቁ አትሌት ሁዋን ሙጉዌራዛ መታሰቢያ ያረገ ሲሆን እኤአ ከ1963 አንስቶ ዓለም አቀፍ ደረጃውን ጠብቆ የዓለም ታላላቅ አትሌቶችን ማፎካከር ችሏል።

በዚህም ኢትዮጵያዊው ታሪካዊ አትሌት ማሞ ወልዴ በወንዶች አሸናፊ በመሆን ከስፔናውያን ውጪ ውድድሩን ያሸነፈ የመጀመሪያ አትሌት መሆን ችሏል። አንጋፋው የኦሊምፒክ ጀግና አትሌት ማሞ ወልዴ በ1967 እና 1968 ይህን ውድድር ለተከታታይ ሁለት ጊዜ በማሸነፍ የማይረሳ ታሪክ መስራት ችሏል።

በዚህም ማሞ ሁሌም በዚህ ውድድር የማይዘነጋ አትሌት መሆን የቻለ ሲሆን ስፔናውያንም ለእርሱ በተለይ በግዛቷ ውስጥ ልዩ ቦታ እንዲሰጡት አድርጓል። ይህንንም በማሰብ አራት የአገር አቋራጭ ውድድር ባለድል በሆነባት ከተማ ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየ በኋላ በግዛቷ ሲወዳደር የሚያሳይ በአልሙኒየም የተሰራ ሃውልት አኑረውለታል።

ከማሞ በኋላም በርካታ ታሪካዊ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በዚህ ውድድር አሸናፊ ሆነው መውጣት ችለዋል። ፊጣ ባይሳ፣ አዲስ አበበ፣ ቀነኒሳ በቀለ፣ ታሪኩ በቀለ፣ ስለሺ ስህን፣ አየለ አብሽሮ፣ ሰለሞን ባረጋ በወንዶች ድል ያደረጉ አትሌቶች ናቸው። በተመሳሳይ በሴቶች ደራርቱ ቱሉ፣ ቁጥሬ ዱሌቻ፣ ገነት ገብረጊዮርጊስ፣ መስታወት ቱፋ፣ ውዴ አያሌው፣ ይመናሹ ታዬ፣ ገለቴ ቡርቃ፣ ህይወት አያሌው፣ ሰንበሬ ተፈሪ የውድድሩ አሸናፊ ሆነው የሚጠቀሱ አትሌቶች ናቸው።

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
Ethiopian Cooperative Commission
(ECC)
ከኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ጋር በመተባበር
በየሳምንቱ የሚታተም

# የአዲስ አበባ የምርት ገበያን በማረጋጋት ትልቅ ድርሻ ያለው ሞዴል ኅብረት ሥራ ማኅበር

**በአስምነህ ቸርነት**

በአዲስ አበባ ኮልፌ ቀራንዮ ካራ ወረዳ 2 መቀመጫውን አድርጎ የተቋቋመ መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር ነው:: ጨፌ ወጣቶች ሁለገብ ኃላፊነቱ የተወሰነ የኅብረት ሥራ ማህበር በግብርናው መስክ በመሰማራት የግብርና ምርቶችን፣ የቁም እንስሳትና ተዋጽኦ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን አምርቶ በቀጥታ ለማህበረሰቡ ተደራሽ በማድረግ የአገራችንን የምርት ግብይት ለማረጋጋት፣ ወጣቱ ማህበረሰብ በኢኮኖሚ እራሳቸውን ችለው እንዲኖሩ ስራ ፈጣሪ ለማድረግና አባላትን የቤት ባለቤት በማድረግ ከመኖሪያ ቤት እጦት ችግር እንዲላቀቁ ለማስቻል ዓላማውን አድርጎ በወርሃ ግንቦት 2012 ዓ.ም የተቋቋመ ኅብረት ነው::

ማህበሩ ለአርሶና አርብቶ አደሩ መኖ በማቅረብና ለግብርና ግብዓቶች ግዢ የሚውል ብድር በማመቻቸት ድጋፍ ይሰጣል:: ለበርካታ ወጣቶችና ሴቶች የስራ እድል በመፍጠር ራዕዩን ለማሳካት በትጋት እየተንቀሳቀሰ የሚገኝ ነው:: በ150 ሺ ብር መነሻ ካፒታል ስራ የጀመረው ጨፌ ወጣቶች ሁለገብ ኃላፊነቱ የተወሰነ የኅብረት ሥራ ማህበር ከሁለት ዓመት ተኩል ባልዘለለ አጭር ዕድሜ ውስጥ አጠቃላይ ካፒታሉን 400 ሚሊዮን ብር ማድረስ የቻለ ሞዴል የኅብረት ሥራ ተቋም ለመሆን የቻለ ነው::

ከ12 ሺ 500 በላይ አባላት ያለው ይህ ኅብረት ስራ ማህበር በግብርና መስክ የስጋ ከብት፣ ፍየልና በግ ማደለብና ማቅረብ፣ እንጀራና ዳቦ ማምረትና ማከፋፈል፣ የከብት ወተትና ወተት ተዋጽኦ ማምረትና ማቅረብ፣ የጥራጥሬና እህል ምርቶችን ማምረትና ማከፋፈል እና አትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ማከፋፈል አገልግሎቶች እየሰጠ የሚገኝ ነው:: በመዝናኛ





ክበብም በአዲስ አበባ ከተማ አገልግሎት ይሰጣል:: ጨፌ ወጣቶች ከኦሮሚያ ክልል ባሻገር በደቡብ ምዕራብ ክልል በቤንች ሸኮ ዞን እና በአማራ ክልል በከሚሴ ወረዳ ካሉ ወጣቶች ጋር በመሆን እየሰራ ይገኛል::

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በእሁድ ገበያ ለሸማቹ ማህበረሰብ በቀጥታ ምርቶች ተደራሽ እንዲሆኑ በማድረግ ከፍተኛ ድርሻ ያለው ኅብረት ስራ ማህበሩ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ጀሞ ቁጥር አንድ በሚገኘው በጀሞ ሁለገብ የገበያ ማዕከል አንድ መጋዘንና 12 ሱቆች እንዲሁም በኮልፌ ቀራኒዮ አንድ ሱቅ ከፍቶ ምርቶቹን ለአዲስ አበባ ነዋሪዎች እያቀረበ ይገኛል:: በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በ121 ወረዳዎች በሚገኙ የኅብረት ሥራ የገበያ ማዕከላት በየሳምንቱ ምርቶቹን ከማቅረብ በተጨማሪ በአዲስ አበባ መውጫና መግቢያ አምስት በሮች ማለትም በሰበታ፣ ሆለታ፣ ገላን፣ ለገጣፎና ሱሉልታ የግብርና ምርቶቹን በማቅረብ ላይ ነው::

በዓላት አለፈም አላለፈም የዋጋ ጭማሪ ያለ ምንም ምክንያት እንዳይኖር እየሰራን ነው የሚሉት የማህበሩ ፕሬዚዳንት አቶ ሰኒ ኢደሹ፤ ኅብረት ስራ ማህበሩ ሸማቹ ማህበረሰብና አባላት አቅሙን ባገናዘበ ሁኔታ በተመጣጣኝ ዋጋ መግዛት እንዲችል የግብርና ምርቶችን፣ የቁም እንስሳት፣ ዶሮና እንቁላል በስፋት በማቅረብ ዋጋ የማረጋጋት ስራ እያከናወኑ መሆናቸውን ይገልጻሉ በቅናሽ ዋጋ ጤፍ እስከነ ወፍጮው በኪሎ 52 ብር፣ ቀይ ጤፍ በኪሎ እስከ 42 ብር፣ ምስር ከ90 - 100ብር፣ ቀይ ሽንኩርት ከደረጃ 1 እስከ 3 በኪሎ ከ12-18 ብር፣ ነጭ ሽንኩርት በኪሎ 90 ብር፣ ዶሮ ከ300 - 350 ብር፣ እንቁላል 8 ብር ከ50፣ ፍየል ከ3 ሺ - 5 ሺ ብር እንዲሁም ስንዴ፣ ሩዝና ሌሎች ምርቶች በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ኃላፊነታቸውን እየተወጡ ናቸው::

ወጣት ሰላማዊት በጋሻው በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ለቡ አካባቢ ነዋሪ ናት:: በጀሞ ሁለገብ የገበያ ማዕከል ጤፍ ለመግዛት የመጣችው ሰላማዊት፤ ከሌላ ቦታ በተሻለ ደረጃ የምርት ዋጋ በጣም በቅናሽ ዋጋ የሚያቀርብና ከአስር ኪሎ በታች ምርት ለሚፈልጉ ሰዎች የሚሸጥ በመሆኑ ተመራጭ ነው ትላለች:: ደንበኝነቷን ከጨፌ ወጣቶች ሁለገብ ኅብረት ሥራ ማህበር ጋር ማድረጓን የምትገልጸው ሰላማዊት፤ አገልግሎታቸው እስካልተቀየረ ድረስ ወደ ማዕከሉ እየመጣሁ ምርቶች መግዛቴን እቀጥላለሁ ስትል ታስረዳለች::

ጨፌ ወጣቶች ሁለገብ ኅብረት ስራ ማህበር ወጣት አባላቱ ኢኮኖሚያዊ አቅማቸውን እንዲገነቡ የገበያ ማዕከላት የመገንባት ስራ እያከናወነ ሲሆን በማህበራዊ አገልግሎት ትምህርት ቤት በመገንባት ኃላፊነቱን እየተወጣ ይገኛል:: በዚህም መሰረት በከሚሴ በአምስት መቶ ካሬ ሜትር ላይ የገነባው ትምህርት ቤት፣ በአምቦ የከፈተው አንድ የገበያ ማዕከል፣ በሌመን ምስራቅ ሸዋ ዞን የገነባው አንድ መጋዘንና አንድ የገበያ ማዕከል በምሳሌነት መነሳት የሚችሉ ናቸው::

የገበያ ክፍተቶችን ለመፍታትና ሌሎች የማህበረሰቡን መሰረታዊ ችግሮች ለመቅረፍ በወጣቶች ተመስርቶ በአጭር ግዜ ውስጥ በተለያዩ አገራችን ክፍሎች ተደራሽ ለመሆን የበቃው ጨፌ ወጣቶች ሁለገብ ኅብረት ስራ ማህበር የእስከ አሁኑ ግዜ ጥረቱ በሞዴልነት የሚወሰድ በመሆኑ ይሄን መሰል ኅብረት ሥራ ማህበር በሌሎች አካባቢዎችም ማስፋት አስፈላጊ ነው::

በ2012 ዓ.ም ተመስርቶ ሞዴል ኅብረት ስራ ማኅበር ለመሆን የበቃው ጨፌ የወጣቶች ሁለገብ ኅብረት ስራ ማኅበር ለገና በዓል ከአባላት ያሰባሰባቸውን የግብርና ምርቶች፣ የቁም እንስሳት፣ የእንስሳት ተዋጽኦዎች እና የኢንዱስትሪ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለአባላትና ማህበረሰቡ አቅርቧል::

አድራሻ | የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኮሚሽን | 0115573448/ 0118592105 | ፖ.ሳ.ቁ. 19787 | Facebook: Federal cooperative Agency | Website: www.fca.gov.et